# "የጦር ሜዳ ውሎ" በተሰኘው የብርጋዴል ጄኔራል ተስፋዬ ኃብተማርያም መጽሐፍ ላይ ከግለ-ታሪክ አጻጻፍ አንጻር የተደረገ ትንተና

በ
እታፈራሁ በየነ

ለአርት ባችለር ዲግሪ ማሟያ
የቀረበ ጥናት

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል
ሰኔ 2001 ዓ.ም.

# “የጦር ሜዳ ውሎ” በተሰኘው የብርጋዴል ጄኔራል ተስፋዬ ኃብተማርያም መጽሐፍ ላይ ከግለ-ታሪክ አጻጻፍ አንጻር የተደረገ ትንተና

በ
እታፈራሁ በየነ

አማካሪ
ብርሃኑ ገ/ማርያም /አቶ/

ለአርት ባችለር ዲግሪ ማሟያ
የቀረበ ጥናት

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል
ሰኔ 2001

# ምስጋና

በመጀመሪያ ይህንን ትምህርት አስጀምሮ ላስጨረሰኝ ለቸሩ መድኃኔዓለም ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡ ቀጥሎ ይህ ጥናታዊ ጽሑፉ ከጅምሩ እስከ ማጠቃለያው ድረስ ከግቡ ይደርስ ዘንድ ውድ ጊዜያቸውን በመሰዋት ሙያዊ አስተያየትና እርማት እየሰጡ ላበረታቱኝና ላገዙኝ አማካሪዬ አቶ ብርሃኑ ገ/ማርያም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

በተጨማሪም ይህንን ትምህርት ጀምሬ እስካጠናቅቅ በሃሳብና በገንዘብ ለረዱኝ ለእናቴ ወ/ሮ በላይነሽ ወርቁ፣ ለወንድሞቼ ለአቶ ደረጄ በየነ፣ ለአቶ ኤርሚያስ በየነና ለአቶ ይትረፍ ድንበሩ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡ በመጨረሻም ይህንን ጥናታዊ ጽሑፍ በቅንነት በኮምፒውተር ለጻፈችልኝ ለወ/ሪት ሜላት አድማሱ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

# አበርክቶ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ መታሰቢያነቱ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ከ1995 – 1999 ዓ.ም. አብረውኝ ይሰሩ ለነበሩ የተማሪዎች ምግብ ቤት ሰራተኞች በሙሉ ይሁንልኝ፡፡

# ማውጫ


ማውጫ ገጽ

**ምዕራፍ አንድ**

**መግቢያ ---------------------------------------------------------------------------------------1**

1.1 ስበበ ጥናት --------------------------------------------------------------------- 1

1.2 የጥናቱ ዓላማ ------------------------------------------------------------------ 2

1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት---------------------------------------------------------------- 2

1.4 የጥናቱ ወሰን -------------------------------------------------------------------- 2

1.5 የአጠናኑ ዘዴ ------------------------------------------------------------------- 2

1.6 በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው --------------------------- 3

1.6.1 ችግሮች ------------------------------------------------------------------ 3

1.6.2 መፍትሄዎች -------------------------------------------------------------- 3

**ምዕራፍ ሁለት**

**ክለሳ ድርሳናት --------------------------------------------------------------------------------4**

2.1 ትወራዊ ደራ----------------------------------------------------------------------- 4

2.1.1 የሕይወት ታሪክ ምንነት ----------------------------------------------- 4

2.1.2 የሕይወት ታሪክ ዓይነቶች---------------------------------------------- 4

2.1.3 የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ ------------------------------------------------ 5

2.1.4 የግለ-ታሪክ ምንነት ---------------------------------------------------- 6

2.1.5 የግለ-ታሪክ አጻጻፍ ----------------------------------------------------- 7

2.1.6 ግለ-ታሪክ ሲጻፍ መካተት ያለባቸው መሰረታዊ ነጥቦች ------------- 8

2.1.7 በሕይወት ታሪክና በግለ-ታሪክ መሐከል ያለ አንድነትና ልዩነት---- 8

2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ------------------------------------------------------------ 9

2.3 የዚህ ጥናት እና የተዛማጅ ጽሑፎች ዝምድና ------------------------------------ 12

2.3.1 ተመሳስሎ-------------------------------------------------------------------- 12

2.3.2 ልዩነት------------------------------------------------------------------------- 13

**ምዕራፍ ሦስት**


**የግለ ታሪኩ የአጻጻፍ ባህሪ ትንተና ---------------------------------------------------------14**

3.1 የግለ-ታሪኩ አጠቃላይ መረጃ ------------------------------------------------------ 14

3.2 የታሪኩ ይዞታ በአጭሩ (አጽመ ታሪክ) ---------------------------------------------- 14

3.3 ታሪኩ ከግለ-ታሪክ አጻጻፍ መርህ አንጻር ------------------------------------------ 16

3.3.1 ከተነባቢነት አንጻር ----------------------------------------------------- 16

3.3.2 ከመረጃ አቀራረብ አንጻር ------------------------------------------------ 22

3.3.3 ከትክክለኛነት አንጻር --------------------------------------------------- 23

3.3.4 ከተአማኒነት አንጻር ---------------------------------------------------- 28


**ምዕራፍ አራት**

**ማጠቃለያና ጥቆማ**


4.1 ማጠቃለያ ------------------------------------------------------------------- 31

4.2 ጥቆማ ---------------------------------------------------------------------- 33

- ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው
- ዋቢ መጻሕፍት

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

የአንድ ሰው የሕይወት ታሪክ ማጥናት ብዙ ጊዜያት እና በቂ ችሎታ የሚጠይቅ በመሆኑ አጥኚው ስለባለታሪኩ ያካበተውን ዕውቀት ተግባራዊ ለማድረግ ጠንቃቃ መሆን አለበት፡፡ በተለይም በሀገራችን ኢትዮጵያ የዚህ ዓይነቱ ጥናት በጣም የተለመደ አይደለም፡፡ አልፎ አልፎ የተጻፈ ነገር እንኳን ቢገኝ የነገስታት ታሪክ ወይም የሰማዕታት ገድል ሆኖ በቤተክርስቲያን ሰዎች የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ብዙ ለሀገራቸው የደከሙና ለወገኖቻቸው መስዋዕትነት የሆኑ ሰዎች የሕይወት ታሪካቸው ሳይታወቅ ቆይቷል፡፡

ግለ-ታሪክ አንድ ግለሰብ የራሱን ታሪክ ከትውልዱ ከአስተዳደጉ ከቤተሰቡና ከስራው ጋር አጣምሮ በማቅረብ ስለማንነቱ ተጨባጭ፣ ግልጽ እና ቀላል በሆነ መንገድ ሌሎች ወገኖች እንዲረዱት የሚያደርግበት የሕይወት ታሪክ ክፍል ነው፡፡ ስለዚህ ባለታሪኩ ግለታሪኩን ከማቅረቡ በፊት ሊያስብባቸው ከሚገቡ መሠረታዊ ጉዳዮች አንዱና ዋናው ታሪኩ በእውነተኛ መረጃ ላይ የተመሠረተ ስለመሆኑ ነው፡፡

አጥኚዋ ይህ የጹሑፍ ዘርፍ በሀገራችንም መስፋፋት እንዳለበት ታምናለች፡፡ በበኩሏ አንድን የታተመ ግለ-ታሪክ ባሕሪያት ለመፈተሽ ጥረት አድርጋለች፡፡

## 1.1. ሰበበ ጥናት

የዚህን ጥናት ርዕስ እንድመርጥ ያነሳሱኝ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ❖ በሀገራችን የራስን ሕይወት ታሪክ (ግለ-ታሪክን) ጽፎ ለትውልድ ማስተላለፍ ያልተለመደ መሆኑ፣
- ❖ ተጽፈው የተገኙት ግለ-ሪኮች ደግሞ በቁጥር አነስተኛ ሆነው መገኘታቸውና
- ❖ አብዛኛዎቹ ተዘጋጅተው የተቀመጡት ግለታሪኮች በታዋቂ ሰዎች እና በነገሥታት ታሪክ ላይ ብቻ አትኩረው መጻፋቸው፣
- ❖ ባለታሪኮቹ በመሠረቱ ነገሥታትና ታላላቅ ሹማምንት ብቻ አለመሆናቸውን ለማመልከት ስለፈለግሁ፡፡

## 1.2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓላማ ብርጋዴል ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተማርያም በጻፉት "የጦር ሜዳ ውሎ" በተሰኘው ግለ ታሪክ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበው ታሪክ፤

ሀ. ተነባቢነቱን ምን ያህል እንደሆነ ማሳየት

ለ. የመረጃ አቀራረቡን አግባብነት መመርመር፣

ሐ. ትክክለኛነቱን/እውነተኛነቱን በመስኩ መርህ መሠረት መግለጽና

መ. ተአማኒነቱን ፈትሾ ማመልከት ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት

በሚከተሉት ምክንያቶች ይህ ጥናት አስፈላጊ (ጠቃሚ) ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡

- ግለታሪክ ሲጻፍ በእውነተኛ መረጃ ላይ መመስረት እንዳለበት ስለሚጠቁም፣
- ግለታሪክ በታዋቂ ሰዎች እና በነገስታት ታሪክ ላይ ብቻ ማተኮር እንደሌለበት ፍንጭ ስለሚሰጥ፣
- የግለታሪክ አዘጋጃጀትን በስፋት እና በጥልቀት ማጥናት ለሚፈልግ ሰው ጥቂት የመነሻ ሃሳብ ሲለሚፈነጥቅ፣
- ግለታሪክ እንዴት ይዘጋጃል? ለሚለው ጥያቄ መሠረታዊ የሆነ ምላሽ ስለሚሰጥ፡፡

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የተካሄደው በብርጋዴል ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተማርያም በ1997 ዓ.ም. "የጦር ሜዳ ውሎ" በሚል ርዕስ በተጻፈው ግለታሪክ ላይ ያተኩራል፡፡ ጥናቱ በተለይ ታሪኩን በግለታሪክ መመዘኛ መስፈርቶች መሰረት ፈትሾ ተነባቢነቱን፣ የመረጃ አቀራረቡን፣ ትክክለኛነቱን እና ተአማኒነቱን ያመለክታል፡፡

## 1.5. የአጠናኑ ዘዴ

በመጀመሪያ ይህንን ጥናታዊ ጽሑፍ ለማዘጋጀት ስነሳ ብርጋዴል ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተማርያም "የጦር ሜዳ ውሎ" በሚል ርዕስ ያዘጋጁትን መጽሐፍ ደጋግሜ ለማንበብ ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ ከዚያም ለጥናቱ የሚሆኑ ንድፈ ሀሳባዊ ጉዳዮችን ከተለየዩ መጻሕፍት ለማግኘት ጥረት አድርጌያለሁ፤ በተጨማሪም ከኢንተረኔትና

ከኢንሳይክሎፒዲያዎች መረጃዎችን ሰብስቤአለሁ፡፡ በመቀጠል ከእኔ ስራ ጋር ተዛማጅነት አላቸው ያልኳቸውን የተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎችን እንደ አስፈላጊነታቸው ተመልክቻለሁ፡፡ በተጨማሪም ከስራዬ ጋረ ተመሳሳይነት ያላቸውን ግለታሪኮች በማንበብ ጥናታዊ ጽሑፌ በመረጥኩት መጽሐፍ ውስጥ ያለውን ታሪክ በግለ-ታሪክ መመዘኛ መስፈርቶች መሰረት እንዴት ተዘጋጅቷል የሚለውን ለመፈተሽ ሞክሬያለሁ፡፡

## 1.6. በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው

ይህንን ጥናታዊ ጽሑፍ በማዘጋጅበት ጊዜ የተለያዩ ቀላልና ከባድ ችግሮች የገጠሙኝ ሲሆን እነዚህን ችግሮች መፍትሄ ይሆናሉ ብዬ ባሰብኳቸው ነገሮች ለመፍታት ጥረት አድርጌያለሁ፡፡

### 1.6.1 ችግሮች

- ✓ ሥራዬ መምህር በመሆኑ የሥራ መደራረብ መከሰቱ፣
- ✓ ለጥናቱ የሚያስፈልጉኝን ነገሮች ለማግኘት ገንዘብ ያጠረኝ መሆኑ፣
- ✓ ጥናቱን በማጠናበት ወቅት ያጋጠመኝ ህመምና፣
- ✓ ለጥናቱ የሚያገለግሉ መረጃ መጻሕፍት በብዛት አለመኖሩ፣

### 1.6.2 መፍትሔዎች

- ✓ የሥራ መደራረብን ለመቀነስ ኃላፊዎችን ፍቃድ በመጠየቅ፣
- ✓ የገጠመኝን የገንዘብ እጥረት ደግሞ ወንድሞቼ እንዲያግዙኝ በማድረግ፣
- ✓ ላጋጠመኝ ሕመም ሐኪም ቤት በመሄድና መድኃኒት በመውሰድ፣
- ✓ የመረጃ መጻሕፍትን ከኢንተርኔትና የተለያዩ ሰዎችን በመጠየቅና በማፈላለግ ለችግሮቼ መፍትሔ አግኝቻለሁ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. ትወራዊ ዳራ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ ንድፈ ሃሳባዊ ጉዳዬችን ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች በመሰብሰብና በማጠናቀር አቅርቤአለሁ፡፡ እነዚህም ሃሳቦች በመረጃ ፍተሻዬ ውስጥ ጠቃሚ መሠረቶች እንደሚሆኑኝ በማመን ነው፡፡

### 2.1.1. የሕይወት ታሪክ ምንነት

"የሕይወት ታሪክ አንድ ሰው ከተወለደበት ዘመን እስከ ዕለተ ሞቱ ወይም እስከ አንድ የተወሰነ ዕድሜው ድረስ የሚተርክ የጽሑፍ ዓይነት ነው፡፡" (ደረጀ ገብሬ፣ 1996 ገጽ 140) የሕይወት ታሪክ አቀራረቡ ግለሰቡ የተጓዘበትን የሕይወት ጉዳናዎች በመረጃ አስደግፎ በማሳየት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህም ሲባል ባለታሪኩ ከልጅነቱ ጀምሮ ታሪኩ እስከ ተዘጋጀበት ዕለት ድረስ ያለፈባቸውን ጉዳዮች የሚያጠቃልል ስለሆነ አንባቢ ጠቅለል ባለ መልኩ ስለባለታሪኩ ዕውቀት፣ ባህሪ፣ ስብዕናና አመለካከት ግንዛቤ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ይህንንም ሃሳብ በተመለከተ ካምብሪጅ ኢንሳይክሎፒዲያ፣ /1994፣147/ ሲገልጽ፡-

> የሕይወት ታሪክ አንድ ሰው ከማን፣ መቼ፣ የት ተወለደ፣ ምን ሠራ፣ በምንስ መንገድ ተጉዞ አሁን ያለበት ደረጃ ደረሰ፣ ወይም አለፈ የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስና ስራዎቹን ማወቅና ማንበብ ለሚሹ ተደራስያን ዘግቦ ለማቆየት የሚጻፍ ነው፡፡ ዘገባውም በሕይወት ባሉ ወይም በሌሉ ላይ ይጻፋል ብሏል፡፡

### 2.1.2. የሕይወት ታሪክ ዓይነቶች

የሕይወት ታሪክ እንደ ጸሐፊዎቹ ማንነት በሁለት ይከፈላል፡፡ የመጀመሪያው አንድ ደሐፊ የራሱን የሕይወት ታሪከ ጽፎ ከተገኘ ግለሕይወት ታሪክ (Auto — Biography) ሲባል ሁለተኛው ደግሞ አንድ ጸሐፊ የሌላን ሰው የሕይወት ታሪከ ከተለያዩ ሰዎች እና መረጃዎች አሰባስቦ የጻፈው ሆኖ ሲገኝ የሕይወት ታሪክ (Biography) ይባላል፡፡ (ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ፣ 1993፣222) ግለታሪክም ሆነ የሕይወት ታሪክ የራሳቸው የሆነ ድክመት እና ጥንካሬ አሏቸው፡፡ ይኸውም ግለ-ታሪክ

ባለታሪኩ የራሱን ታሪክ የሚጽፍ መሆኑ ስለራሱ ያለውን እውነታ ዘርዝሮ ሊጽፍ ይችላል፡፡ በዚህም የሚጐድል መረጃ አለመኖሩ ጥንካሬውን ሲያሳየን፣ ባለታሪኩ ድክመቶቹን በመሸፋፈን ጥንካሬዎቹን በማጉላትና ታሪኩን አድሎአዊ እንዲሆን ሊያዳርገው የሚችል በመሆኑ በዋናነት ሊጠቅስ የሚችል ደካማ ጐን ነው፡፡

የሕይወት ታሪክ ጸሐፊው የሌላን ሰው ታሪክ የሚጽፍ በመሆኑ የተለያዩ መረጃዎችን በማገላበጥና እውነታዎችን በማመዛዘን ትክክለኛና ሚዛናዊ ስራ ሊያቀርብ ስለሚችል ከግለ-ታሪክ በተሻለ የባለታሪኩን ድክመት እና ጥንካሬ እኩል ያስተናግዳል፡፡ ይህ ጠንካራ ጐኑ ሲሆን አጥኚው በቂ የመረጃ ምንጭ ካላገኘ በተለይም ባለታሪኩ በሕይወት የሌለ ከሆነ የሚጻፈው ታሪክ የተሟላ ላይሆን መቻሉ ድክመት ነው፡፡

## 2.1.3. የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ

አንድ የህይወት ታሪክ በሚጻፍበት ጊዜ እንደፈጠራ ጽሑፍ የራሱን ፈጠራ በመጨመር የግለሰቡን የማህበራዊ ሕይወት ልዩ ልዩ ገጽታዎች የሚንጸባረቅበት፣ በቃላት አማካይነት የሚሳል ምናባዊ የሆነ ጽሑፍ ሳይሆን በእውነተኛ መረጃ ላይ የተመረኮዘ ታሪክ መሆን ይኖርበታል፡፡

የሕይወት ታሪክ በሚጻፍበት ጊዜ በውስጡ አንድ ግለሰብ መቼና የት ተወለደ፣ የቤተሰቦቹንና የአስተዳደጉን ሁኔታ፣ የተማረበትን ወይም ያከናወናቸውን ድርጊቶች እና የተሳተፈበትን ሙያ አጠቃሎ የሚይዝ መሆን አለበት፡፡

የአንድን ግለሰብ ህይወት ታሪክ ጸሐፊው በሁለት መንገዶች ሊያቀረብ ይችላል፡፡ ይኸውም የመጀመሪያ የሚሆነው ባለታሪኩ በሕይወት እያለ የሚጻፍ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በህይወት ሳይኖር የሚጻፍ ተብለው ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ በሕይወት ሳይኖር የሚጻፈው መረጃ ለማግኘት ስለባለታሪኩ የሚያውቁ ሰዎችን በመጠየቅ፣ ቤተሰብ፣ ጓደኞችንና ከራሱ የግል ማስታወሻ እንደመነሻ በመጨመር የሚቀርብ ሲሆን በሕይወት ላለ ባለታሪክ ግን መረጃ በሁለት መልክ ማግኘት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ከላይ በተገለጸው መሠረት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ግለሰቡን ፊት ለፊት በመጠየቅ የበለጠና ሰፋ ያለ መረጃ ማግኘት ነው፡፡

የሕይወት ታሪክ አቅጣጫው በእውነታ ላይ የተመሰረተ ግለሰባዊ የሆነ መረጃ መስጠት በመሆኑ የፈጠራ ስራ እዚህ ውስጥ ቦታ የለውም፡፡ ምክንያቱም የሕይወት

ታሪክ ኢ-ልቦለዳዊ የስነ-ጽሑፍ አካል ሲሆን የሚያነሳውም የአንድን ግለሰብ ጉዳይ ነው፡፡ ግለሰቡ ስለራሱ የጻፋቸውን ግለ-ታሪኮችንም ይይዛል፡፡

### 2.1.4. የግለ ታሪክ ምንነት

አንድ ግለሰብ የራሱን የሕይወት ገጠመኝ በጽሑፍ አዘጋጅቶ ማቅረብ ይችላል፡፡ ታዲያ የግለሰቡ ታሪክ በባለታሪኩ በራሱ ተዘጋጅቶ ስናገኝ ስራው ግለታሪክ ይባላል፡፡ በተጨማሪም ግለሰቡ የራሱን ታሪክ ከትውልዱ፣ ከአስተዳደጉ፣ ከቤተሰቡና ከሥራው ጋር ተጨባጭ ግልጽ እና ቀላል በሆነ መንገድ የሚያሳይበት ጸሑፍ ነው፡፡ ይህንንም በማስመልከት ሳህለስላሴ ብርሃነማርያም ከገጽ 83 — 84 የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> ማንኛውም ሰው የሕይወት ታሪኩን ለመጻፍ ይችላል፡፡ እንዳይጽፍ የሚያግደው ሕግ የለም፡፡ ሆኖም ብዙ ጊዜ ሲደረግ እንደምናየው የሕይወት ታሪካቸውን የሚጽፉት ታላላቅ የፖለቲካና የጦር መሪዎች፤ በሳይንስ፣ በስነ-ጥበብና በልዩ ልዩ የዕውቀትና የሙያ ዘረፎች ለአገራቸውም ሆነ ለመላው ዓለም ሕብረተሰብ ጉልህ አስተዋጽኦ ያደረጉ፣ እንዲሁም . . . ሕይወት ታሪካቸውን የሚጽፉ ሰዎች በአብሪት ተነሳስተው “ታላቅነታቸውን” ለማሳየት ሳይሆን ታላቅ ሥራቸው ለሌሎች አብነት እንዲሆንና በተለይም ወጣቱ ትውልድ ለታላቅ ሥራ እንዲነሳሳ ለማድረግ ነው፡፡ የሕይወት ታሪካቸውን የሚጽፉ ሰዎች እውነተኛ ታሪካቸውን በተሟላና በሚያሳምን ሁኔታ ሲያቀርቡት የአንባቢያንን አድናቆት እንደሚያተርፉ ሁሉ ባልተሟላና በማያሳምን ሁኔታ ሲያቀርቡት በአንባቢያን ዘንድ ቅሬታ ይፈጥራል፡፡

ግለ-ታሪክ በራስ የሕይወት ገጠመኝ ዙሪያ የሚሽከረከር ታሪክ እንደመሆኑ ማንኛውም ነገር የሚያቀርበው በባለታሪኩ እይታ ነው፡፡ ስለዚህ በእንዲህ ዓይነቱ ጽሑፍ ራስን ከፍ ከፍ የማድረግ፣ ከተጠያቂነት የመሸሽ እና እራስን ለመተቸት አለመድፈር ጐልተው ይታያሉ፡፡

ግለ-ታሪኮች እንደ ሕይወት ታሪኮች ሁሉ ስለ ታላላቅና ታዋቂ ሰዎች ማንነት በቂ ግንዛቤ ለአንባቢዎች በመስጠት ስለሰዎቹ ያለንን የማወቅ ጉጉትና ጥልቅ ፍላጐት ለማርካት ከማስቻላቸውም በላይ ለታሪክ ጥናት የሚረዱ መሰረታዊ የመረጃ ምንጮች ናቸው፡፡ በተጨማሪ ግለ-ታሪኮችም ልክ እንደ ሕይወት ታሪክ ጸሐፊው ጽሑፉን ከመጻፉ በፊት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በብቃት ማሰባሰብ ይኖርበታል፡፡

አንድ ሰው የራሱን የሕይወት ታሪክ በሚያዘጋጅበት ጊዜ በተቻለ መጠን የሚጠቀማቸው ቃላት ለአንባቢው ግልጽ የሆኑ እና ግራ የማያጋቡ መሆን

ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም ቃላቶቹ ግልጽ እና በቀላል ለአንባቢ የሚገቡ ካልሆኑ ግለ-ታሪኩ ተነባቢነቱን ሊያጣ ስለሚችል ነው።

አንድ ግለ-ታሪክ ሲጻፍ በመጀመሪያ በእውነተኛ የራስ ታሪክ ላይ መመስረት ይኖርበታል። ይህም ሲባል ባለታሪኩ የትና መቼ እንደተወለደ? የት እንደሚኖር? የት እንደተማረና ከማን ጋር እንደሚኖር የመሳሰሉትን በአግባቡ መግለጽ አለበት። በዚህም አንባቢው ስለ ባለታሪኩ ትክክለኛ የሆነ ሙሉ መረጃ እንዲኖረው ያደርጋል።

## 2.1.5. የግለ ታሪክ አጻጻፍ

ግለታሪክ ለመጻፍ በመጀመሪያ ሦስት ነገሮችን ማወቅ አለብን። ስለዚህ ጉዳይ /hptt//www. Writers services.com /mag/05/ Writing Bio-auto-bio. /htm የተባለው ድኅረ-ገጽ የመጀመሪያው እኛ ማን እንደሆንን መገንዘብ ሲሆን ሁለተኛው ሕይወት ለኛ ምን እንደሆነ በወጉ መረዳት እና ሦስተኛው ስለወደፊቱ ሕይወታችን ምን አመለካከት እንዳለ ማጤን የሚሉ ናቸው በማለት ገልጿል።

እኛ ማን እንደሆንንና በሕይወታችን ውስጥ ያሳለፍናቸው ነገሮች ስንል የመጀመሪያ የሚሆነው ስማችንን መጻፍ በመቀጠል ስለራሳችን ማንነት እና ሕይወታችን ውስጥ ስለገጠሙን ነገሮች መጻፍ አለበት። ለምሳሌ በሕይወታችን ውስጥ ባደረግነው ነገር ተሸልመን ከሆነ ምን ዓይነት ሽልማት እንደተሸለምን እና ለወደፊት የምናስበው ዕቅድ ካለንም መካተት አለበት።

ለኛ ሕይወት ምን እንደሆነ ስንል ደግሞ፡- ሕይወት ለኛ ምን እንደምትመስል፣ ምን ማለት እንደሆነ፣ በሕይወታችን ደስተኛ ወይም የምናዝን ከሆነ መጻፍ ይኖርበታል። በተጨማሪም የትምህርት ጊዜያችን እንዴት እንደሆነ፣ ስላሉን ጓደኞች ብዛት እንዲሁም የፍቅር ጓደኛ እንዳለን ወይም እንደሌለንና የመሳሰሉት መካተት ይኖርባቸዋል።

የወደፊት ሕይወታችን ምን እንደሚመስል፡- ደግሞ በሕይወታችን ውስጥ ባለው ጊዜ ውስጥ ሊገጥመን የሚችለውን ነገር በራሳችን አስተሳሰብ መጻፍ አለብን። ለምሳሌ፡- ወደፊት እንዴት እንደምንኖር፣ የት እንደምንኖር፣ መስራት ያሰብነው ነገር ካለ፣ ካላገባን እናገባ ይሆን፣ ልጆች ይኖሩን ይሆን ማንን እናገባ ይሆን? እነዚህንና የመሳሰሉትን በትክክል በእውነተኛ መረጃ ላይ ተመርኩዞ መጻፍ ያስፈልጋል።

### 2.1.6. ግለታሪክ ሲጻፍ መካተት ያለባቸው መሰረታዊ ነጥቦች

አንድ ሰው የራሱን የሕይወት ታሪክ ለማዘጋጀት በሚነሳበት ጊዜ ከዚህ በታች በዝርዝር የሰፈሩትን ነጥቦች ቢያካትት ታሪኩ ተነባቢነትን ያገኛል፡፡ ምክንያቱም አንባቢው ከታሪኩ የሚፈልገውን መረጃ በቀላሉ እንዲያገኝ ይረዱታል፡፡

**የተሪኪው (የባለታሪኩ)**

- ሙሉ ስምና የልደት ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምህረት
- የትውልድ ሀገር፣ ከተማ፣ ወረዳና ልዩ ቀበሌ ስም
- እናትና አባት ስም
- እምነት (ክርስትና፣ እስልምና ወ.ዘ.ተ)
- የህፃንነት ሕይወት
- የትምህርት እና የስራ ላይ ቆይታው
- የትዳር ሕይወት
- በሕይወቱ ያጋጠሙት አሳዛኝ እና አስደሳች ነገሮች
- ያገኛቸው ሹመትና ሽልማቶች
- በሕይወት ዘመኑ ያከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራት
- የጊዜ ማሳለፊያዎቹ
- ስለ ህይወት ያለው አመለካከት
- በሕይወት ዘመኑ ያከናወናቸው በጎ ነገሮች

### 2.1.7. በሕይወት ታሪክ እና በግለ-ታሪክ መሐከል ያለ አንድነት እና ልዩነት

**አንድነት**

- የሕይወት ታሪክም ሆነ ግለታሪክ የአንድን ግለሰብ ድርጊቶች የሚመለከቱ ናቸው፡፡
- ግለ-ታሪክም ሆነ ሕይወት ታሪክ በእውነታ ላይ የተመሰረተ ግለሰባዊ የሆነ መረጃ ይሰጣሉ፡፡
- ግለታሪክም ሆነ ሕይወት ታሪክ አንድ ሰው ከማን፣ መቼ ተወለደ? አሊያም አለፈ? የሚሉትን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

- የሕይወት ታሪክም ሆነ ግለ-ታሪክ ስለአንድ ሰው ሕይወት የሚዘግቡ የታሪክ ዘርፍ ናቸው፡፡
- ግለ-ታሪክም ሆነ የሕይወት ታሪክ በቅድሚያ አስፈላጊ መረጃዎች በብቃት ማሰባሰብ የሚጠይቁ ናቸው፡፡

### ልዩነት

- የሕይወት ታሪክ የአንድን ግለሰብ ድርጊት ከልደት እስከ ሞት ያለውን የሚያጠቃልል ሲሆን ግለታሪክ ግን አንድ ግለሰብ ከልደቱ አንስቶ ታሪኩን እስከአዘጋጀበት ቀን ድረስ የፈጸመውን ድርጊት የሚያጠቃልል ነው፡፡
- የሕይወት ታሪክ ግለ-ታሪኩ በሕይወት ሳይኖር ሊዘጋጅ ይችላል፤ ግለ-ታሪክ ግን ባለታሪኩ በሕይወት እያለ የሚዘጋጅ ነው፡፡
- የሕይወት ታሪክ የአንድ ግለሰብ ታሪክ ሌላ ሰው የሚያዘጋጀው ሲሆን፣ ግለ-ታሪክ በታሪኩ ባለቤት የሚዘጋጅ ነው፡፡

## 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ይህንን ጥናት ለማድረግ ስነሳ ከእኔ ስራ ጋር የተቀራረቡ በርካታ የዲግሪ ሚሚያ ጽሑፎችን በኬኔዲም ሆነ በ ILS ቤተመጻሕፍት አግኝቻለሁ፡፡ ነገር ግን ተሰርተው ያገኘኋቸው ጥናቶች አብዛኛዎቹ የአንድን ሰው የሕይወት ታሪክ እና ስራዎቹን አሰባስቦ በማስቀመጥ ላይ ያተኮሩ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡ ነገር ግን የእኔ ስራ በብርጋዴል ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተማርያም የጦር ሜዳ ውሎ በተሰኘው ግለ-ታሪክ ላይ በግለ-ታሪክ መመዘኛ መስፈርቶች መሰረት ግለታሪኩ እንዴት ተዘጋጅቶ ይገኛል? የሚለውን በመፈተሽ ላይ ያተኮረ በመሆኑ ከእነዚህ ስራዎች በተወሰነ መልኩ የተለየ ቢሆንም ግለ-ታሪክ አንዱ የሕይወት ታሪክ ቅርንጫፍ መሆኑ ያመሳስላቸዋል፡፡ ስለሆነም ለስራዬ ያግዙኛል ያልኳቸውን አራት ዲማጾችን ብቻ በቅርበት ለመቃኘት ሞክሬያለሁ፡፡

ጥላሁን በሻህ፣ "ከ1967 — 1983 ዓ.ም. በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የሕይወት ታሪካቸው የተጻፈላቸው ኢትዮጵያን/ት መዘርዘር" በሚል ርዕስ የመጀመሪያ ዲግሪ ሚሚያ ጽሑፉን በ1989 ዓ.ም አቅርቧል፡፡ ጥላሁን አላማው አድርጎ ያስቀመጠው ከ1967 — 1983 ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ የሕይወት ታሪካቸው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የተጻፈላቸውን ኢትዮጵያውያን/ት ስምና የሕይወት ታሪካቸውን ሰብስቦና ስርዓት

ባለው መንገድ አስፍሮ ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስተላለፍ፤ በተሰጠው የጊዜ ክልል ውስጥ ምን ያህል ኢትዮጵያውያን/ት የሕይወት ታሪክ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ተጽፎ ወጥቷል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በማሰብ ነው በማለት ገልጿል፡፡

የጥላሁን መረጃ አሰባሰብ ዘዴ በተመለከተ ተጠርዘው በቤተ መጻሕፍት የሚገኙ ጋዜጦችን በማገላበጥ ከ1967 — 1976 ዓ.ም የሕይወት ታሪካቸው የተጻፈላቸውን ኢትዮጵያውያን/ት ስም በመሰብሰብ፣ ከ1976 - ግንቦት 15 ቀን 1983 ዓ.ም ድረስ ሰርተው ታወቁ ከሚል ሳምንታዊ አምድ ላይ ታሪኩ የጻፈለት ሰው ሲገኝ ጽሑፉን በማንበብ እና መቼ እንደተወለደ፣ በሕይወት ዘመኑ ምን ምን እንደሰራ፣ መቼ እንደ ሞተ ከጽሑፉ በማውጣት የጋዜጣውን ስም፣ የተጻፈበትን ቀን፣ ወር እና ዓ.ም ከነገጽ ቁጥሩ በመጻፍ አስፈላጊውን መረጃ እንደሰበሰበ ይነገረናል፡፡

ጥላሁን ያገኘውን ግኝት ስንመለከት ደግሞ ጥናታዊ ጽሑፍ ከ1967 — 1983 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የሕይወት ታሪካቸው የተጻፈላቸውን ኢትዮጵያውያን/ት የሚያጠቃልል ሲሆን፣ ይህ የዘመን ክልል ደግሞ የደርግ ዘመን ነበር፡፡ በጽሑፉ ለማየት እንደተሞከረው ከመቶ ሰባስድስቱ ጠቅላላ ቁጥር ሰማንያ አምስቱ አርበኞች ናቸው፡፡ ከዚህም ተነስቶ በዚህ የዘመን ክልል ውስጥ በጦርነት የተሳተፉ አርበኞች የሕይወት ታሪክ እንዲጻፍላቸው መፈቀድ ህዝቡ ወደ አርበኝነት እንዲገፋፋና ከየአቅጣጫው የተነሱትን ተቃዋሚዎች ለመዋጋት እንዲያስችላቸው ነው፡፡ የሚል አንድምታ ላይ እንደደረሰ ይነግረናል፡፡

ብርሃን ክብረት፣ "የአርቲስት አለባቸው ተካን የሕይወት ታሪክ እና ስራዎቹ" በሚል ርዕስ በ1998 ዓ.ም የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፉን ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ክፍል አቅርባለች፡፡ ብርሃን ዓላማ አድርጋ ያቀረበችው የአርቲስት አለባቸው ተካን የሕይወት ታሪክና ስራዎቹን መዳሰስን ነው፡፡ በተጨማሪም አርቲስቱ በሕይወት ዘመኑ የሰራቸውንና ያሳለፋቸውን የሕይወት ገጠመኞች ምን ይመስላሉ? የሚለውን በተናጠልና በዝርዝር ተመልክታለች፡፡ ሌላው የአርቲስቱ ስራዎች ምን ምን ናቸው፡፡ የሚለውንና ሌሎች ንዑሳን የሆኑ ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ተመልክታላች፡፡

ብርሃን ለጥናቷ የሚሆኑ መረጃዎች የሰበሰበችባቸው ዘዴዎች በቃለ መጠይቅ፣ የአርቲስቱን የስራ ባልደረቦችና አድናቂዎች ጋር በአካል በመገናኘት፣ በተለያዩ ጊዜያት ከባለታሪኩ ጋር በመጽሔትና በጋዜጣ ከተደረጉ ቃለ መጠይቆች እንደሆነ ገልጻለች፡፡

ብርሃን የደረሰችበት ግኝት ደግሞ አርቲስት አለባቸው ተካ ከራሱ ይልቅ ለወገኖቹ የሚያስብ ሲቪል ጀግና እንደሆነ እና ሀገራችን እሱን ለመተካት ምናልባት ብዙ ዓመታት መጠበቅ እንደሚኖርባት ጠቂማ አርቲስቱ ሰዎችን ለመጥቀም ሲል ራሱን ረስቶ በሀገራችን ላይ የመረዳዳትና አንዱ ሌላውን የማስተዋል ልማድ በሌሎች ሰዎች እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ በማለት ትገልጻለች፡፡

የትናየት አንዳርጌ "የቀደምት ሴት ጋዜጠኞች የሕይወት ታሪክ እና ሥራዎቻቸው" በሚል ርዕስ በ1989 ዓ.ም የመጀመሪያ ዲግሪ ሚሚያ ጽሑፏን አቅርባለች፡፡ የትናየት ዓላማዋን እንዲህ በማለት አቅርባለች፡፡ "የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ሴት ጋዜጠኞችን የሕይወት ታሪክ እና በሙያቸው ያከናወኑትን ተግባር በማጥናት በታሪክ መዘክርነት ለማስቀመጥ ነው፡፡ የጥናቱ ሌሎች ዓላማዎች ደግሞ በዝርዝር እንደሚከተለው አቅርባለች፡፡

ሀ/ ጋዜጠኞች ለሀገራችን የጋዜጠኝነት ሙያ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ በማሳየት እውቅና እንዲያገኙና

ለ/ ወደፊት በጋዜጠኝነት ሙያ ለመሰማራት የሚፈልጉ ወጣት ሴቶችን ከእነዚህ የሕይወት ታሪክ ልምድ እንዲቀስሙ ማድረግ

የየትናየት የመረጃ አሰባሰብ በተመለከተ ደግሞ መጀመሪያ ሴት ጋዜጠኛ ለነበሩትና አሁን በሕይወት ላሉ በርካታ ጥያቄዎችን አካቶ የተዘጋጀውን መጠይቅ ሞልተዋል፣ የቅርብ ጓደኞቻቸው፣ የስራ ባልደረቦቻቸው የእማኝነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ተጠይቀዋል፡፡ በተጨማሪም አንጋፋ ጋዜጠኞችንና በኃላፊነት ቦታ ላይ የነበሩ ምስክርነት ሰጥተዋል፡፡ ከጋዜጠኞቹም የሕይወት ታሪክ እና ስራዎቻቸው ጋር የተያያዙ መጻሕፍት፣ መጽሔቶች፣ ያልታተሙ ጥራዞች፣ ጋዜጦችን እንዲሁም የዲግሪ ሚሚያ ጽሑፎችን እንደ አስፈላጊነታቸው ተመርምረዋል፡፡ በማለት አመልክታለች፡፡

የትናየት የደረሰችበትን ግኝት ስንመለከት ከ1966 ዓ.ም በፊት ባለው የሴት ጋዜጠኞች ቁጥር አነስተኛ ከመሆኑም በላይ በስራ ልምድ ዝቅተኛ የሚባለውን ቦታ ይዘው ይገኛሉ፡፡ በኃላፊነት ቦታ ላይ የተቀመጡትም አልነበሩም ለዚህም ምክንያት ሴቶች ከወንዶች እኩል አለመታየታቸው፣ የሙያው አለማደግና በነጻነት እንዲሰሩ ሁኔታዎች አለመመቻቸታቸው በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው በማለት ገልጻለች፡፡

ፀጋዬ ገ/ማርያም፣ "የአለልኝ መኳንንት የሕይወት ታሪክ እና ስራዎች" በሚል ርዕስ በ1992 ዓ.ም የመጀመሪያ የዲግሪ ሚሚያ ጽሑፉን አቅርቧል፡፡ የፀጋዬ ዓላማ

የአርቲስቱን የሕይወት ታሪክ እና ስራዎቹን እንዲሁም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ካቀረባቸው ተውኔቶች ውስጥ አንዱን በመውሰድ ትንታኔ መስጠትና ስራዎቹን በተለይ ከጽሕፈተ ተውኔት፣ ከዝግጅት እና ከትወና አንጻር የሚዳሰስ ነው።

የፀጋዬ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ በመጀመሪያ አርቲስቱን በግንባር አግኝቶ ቃለ መጠይቅ ማድረግ፣ ስለ አርቲስቱ በመገናኛ ብዙሀን በተለይም በልዩ ልዩ መጽሔቶችና ጋዜጦች የወጡ አስተያየቶችና ማበረታቻዎችን በማሰባሰብ፣ የተቀረጹ የአርቲስቱን ካሴቶች በመመልከት፣ በተጨማሪም ከሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጭ ከግለሰብ ለአርቲስቱ የተጻፈለትን ደብዳቤዎች ጭምር መመርመር ሲሆን በግኝትነት ደግሞ አርቲስቱ ዝቅተኛ ኑሮ ካለው ማህበረሰብ የሚመደብ እና የሚያነሳቸው ርዕስ ጉዳዮችና የሚቀርጻቸው ገጸ ባህሪያት ሁሉ አስተዳደጉን፣ በውስጡ የነበረውን ስብዕናውን፣ ያደገበትን አካባቢና የሚኖርበትን ማህበረሰብ ኑሮ ደረጃው በግልጽ የሚያሳይ እንደሆነ አመልክቷል።

## 2.3. የዚህ ጥናት እና የተዛማጅ ጥናቶች ዝምድና

በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ እና በተዛማጅ ጥናቶች መካከል ያለውን ዝምድና ከሁለት አቅጣጫዎች ለማየት ጥረት አድርጌያለሁ። ይኸውም በእኔ ጥናት እና በተዛማጅነት በተመረጡ አራት ጥናታዊ ጽሑፎች መካከል ያለውን ተመሳስሎ እና ልዩነት በቅደም ተከተል በማስቀመጥ ላይ ያተኮረ ነው።

### 2.3.1 ተመሳስሎ

በዚህ ጥናት እና በጥላሁን በሻህ ጥናት መካከል ያለው ተመሳስሎ የጐላ ባይሆንም ርዕሳቸው ተመሳሳይ ሆኖ አግኝቻቸዋለሁ። ይኸውም ጥላሁን ከ1967 — 1983 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የሕይወት ታሪካቸው የተጻፈላቸው ኢትዮጵያውያን/ት መዘርዝር የሚል ሲሆን የኔ ደግሞ የብርጋዴል ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተማርያም የጦር ሜዳ ውሎ ከግለታሪክ አጻጻፍ አንጻር የተሰጠ ትንተና የሚል ነው። ስለሆነም ግለ-ታሪክ አንዱ የሕይወት ታሪክ አካል በመሆኑ በርዕሶቹ መካከል ተመሳስሎ እንዲፈጠር አድርጓል።

በሁለተኛ ደረጃ ያየሁት የብርሃን ክብረት ጥናታዊ ጽሑፍ ሲሆን ብርሃን በአርቲስት አለባቸው ተካ የሕይወት ታሪክ እና ስራዎቹ በሚል ርዕስ ጥናቷን ያቀረበች

ሲሆን ይሕንንም ከኔ ጥናት ርዕስ ጋር ሳነጻጽረው ልክ እንደ ጥላሁን ተመሳስሎ አላቸው፡፡

በሦስተኛ ደረጃ ያየሁት የፀጋዬ ገ/ማርያም ጥናታዊ ጽሑፍ ሲሆን ይህም ጥናት ከኔ ጥናት ጋር ከላይ ከተገለጹት ሁለት ጥናቶች በርዕሱ ከመመሳሰል ውጪ ሌላ ተመሳስሎ አላየሁበትም፡፡

በመጨረሻ የትናየት አንዳርጌ ያቀረበችውን ጥናታዊ ጽሑፍ ከኔ ጥናት ጋር ያለው ተመሳስሎ ከሌሎቹ የተለየ አይደለም፡፡ ልክ እንደሌሎቹ የጥናታችን ርዕስ ተመሳስሎ ይታይበታል፡፡

## 2.3.2 ልዩነት

የእኔን ጥናታዊ ጽሑፍና የጥላሁን ጥናታዊ ጽሑፍ ዓላማ ከፍተኛ ልዩነት አላቸው፡፡ ይኸውም የጥላሁን ዓላማ ከ1967 — 1983 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የሕይወት ታሪካቸው የተጻፈላቸውን ኢትዮጵያውያን ስምና የሕይወት ታሪክ ሰብስቦ ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ ሲሆን የኔ ዓላማ ደግሞ የብርጋዴል ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተማርያም ግለታሪክ እንዴት ተዘጋጅቶ ይገኛል? የሚለውን በግለታሪክ መመዘኛ መስፈርቶች መሠረት በመፈተሽ ላይ ያተኮረ እንጂ የግለሰቡን ታሪክ ለትውልድ የማስተላለፍ ዓላማ የለውም፡፡

ሌላው በጥላሁን እና በእኔ ጥናት ያለው ልዩነት የጥላሁን ስራ የሕይወት ታሪክ የኔ ደግሞ ግለታሪክ በመሆኑ በሚጽፋቸው ሰው አማካይነት የተለያዩ ናቸው፡፡

ቀጥሎ የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍና የብርሃንን ዓላማ ስመለከት ከላይ የተገለጸውን ሃሳብ የሚጋራ ነው፡፡

የየትናየትና የፀጋዬንም ጥናታዊ ጽሑፍ ስመለከት በዓላማ እና ታሪኩን በጻፈው ሰው መለያየት ምክንያት የተለያዩ ናቸው፡፡ ማለትም ግለታሪክ ባለ ታሪኩ ራሱ ያዘጋጀው ሲሆን የሕይወት ታሪክ ደግሞ የሌላ ሰውን ታሪክ አንድ ጸሐፊ ያዘጋጀው ስለሆነ በአጻጻፍ ደረጃ የተለያዩ ናቸው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የግለ-ታሪኩ የአጻጻፍ ባህሪ ትንተና

## 3.1 የግለ-ታሪኩ አጠቃላይ መረጃ

- የመጽሐፉ ርዕስ - የጦር ሜዳ ውሎ
- ደራሲው - ብ/ጀኔራል ተስፋዬ ሀብተ ማርያም
- የታተመበት ጊዜ - 1997 ዓ.ም
- ማተሚያ ቤት - አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት
- የገጾች ብዛት - 323
- የምዕራፎች ብዛት - 26
- ደጋፊ መሳሪያዎች - ፎቶግራፎች
  - የምስክር ወረቀቶች
  - ካርታዎች፣ ሠንጠረዦች

## 3.2 የታሪኩ ይዞታ በአጭሩ (አጽመ ታሪክ)

ብርጋዴል ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተማርያም በቀድሞ ሸዋ ክፍለ ሀገር ጨቦና ጉራጌ አውራጃ ቸሀ ወረዳ ውስጥ ልዩ ስሙ ሲሰ ተብሎ በሚጠራው መንደር ከአባታቸው ከአቶ ቆትያ (ሀብተማርያም) ጋና እና ከእናታቸው ወ/ሮ ፈርሸዋት ጋጅወ በ1933 ዓ.ም ተወለዱ፡፡ ለወላጆቻቸው ሦስተኛ ልጅ ናቸው፡፡

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በመጀመሪያ በቄስ ትምህርት ቤት ቀጥሎም ጉብሬ በሚባል ዘመናዊ ት/ቤት ገብተው መማር ጀመሩ፡፡ ነገር ግን ጉብሬ ት/ቤት እስከ 3ኛ ክፍል ብቻ በመሆኑ ቀጣዩን ትምህርታቸውን ለመከታተል ከመኖሪያ ቤታቸው በግምት 25 ኪሎ ሜትር የሚርቅ እምድብር በሚባል ት/ቤት ከ4ኛ - 8ኛ ክፍል ተማሩ፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአምቦ እርሻ ት/ቤት ተከታትለው መልቀቂያ ፈተና ጥሩ ውጤት በማምጣታቸው ዓለማያ እርሻ ኮሌጅ ተመደቡ፡፡ ከምደባ በኋላ ቤተሰቦቻቸውን ለመጠየቅ ወደ አገር ቤት ሄዱ፡፡ እዚያ ሲደርሱ አባቻውን ታመው ስላገኙአቸው እሳቸውን ሲያስታምሙ የኮሌጅ መግቢያ ቀን በማለፉ ትምህርታቸውን ገብተው መማር አልቻሉም፡፡ በዚህ ጊዜ ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ሲያስቡ በድንገት መንገድ ላይየቀድሞ ጓደኛቸውን አግኝተው የገጠማቸውን ሁሉ ነገሩት፡፡ ጓደኛቸው ወደ

ሀገር ቤት ከመሄድ ወደ “አርሚ ኮሌጅ” መግባት እንደሚሻል ስለነገራቸው እዛ ሄደው ተመዝግበው የውትድርና ሕይወታቸውን ጀመሩ፡፡

በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ሀረር ጦር አካዳሚ ለሶስት ዓመታት ትምህርታቸውን ተከታትለው በምክትል ፀአለቃነት ማዕረግ ተመርቀው ከአካዳሚው ወጡ፡፡ ከአካዳሚው እንደወጡ የገቡት በደብረ ዘይት አየር ወለድ ተጨማሪ ስልጠና ለመውሰድ ነበር፡፡ ይህን ስልጠና ሲጨርሱ 3ኛ ክፍለ ጦር 25ኛ ሻለቃ ወደሚገኝበት ኦጋዴን ልዩ ስሙ ደገሃቡር የሚባል ቦታ ተመድበው ሄዱ፡፡ በዚያም የመቶ መሪ ሆነው ተመደቡ፡፡

የመቶ መሪ ሆነው ከተመደቡ በኋላ የመጀመሪያ ስራቸው የ3ኛውን ክፍለ ጦር ለአሰሳ ይዞ መውጣት ነበር፡፡ ለአሰሳ በወጡበት ጊዜም የደረሰባቸውን ጥቃት በአሸናፊነት በመወጣት ተመልሰው መጡ፡፡ ስራቸውም በዚህ ተጀመረ፡፡

ብርጋዴል ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተማርያም ስድስት ወር ያህል ደገሀቡር ከቆዩ በኋላ የእስፔሻል ፎርስ ስልጠና በድሬደዋ በእስራኤሎች ወስደዋል፡፡

በኢትዮጵያና በሶማሊያ መካከል በነበረው አለመግባባት በ1970 ዓ.ም በተደረገው ጦርነት አሸናፊ በመሆን አጠናቀዋል፡፡ በተጨማሪም በኢትዮጵያ አየር መንገድ ላይ የነበረውን የበረራ ጥቃት ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን የበረራ ደህንነት ጥበቃን በማከናወናቸው የምስጋና ደብዳቤ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በናቅፋ ዘመቻ ውይይትና የናቅፋ ዝላይ አፈጻጸም ላይ ተሳትፈዋል፡፡

ከሻቢያ ጋር በነበረ ውጊያ ጦም ውሎ ማደርን፣ ትጥቅን ከላይ ላይ ሳይፈቱ ጫማ ሳያወልቁና ቅማልና ቁንጫ እየበላቸው ትግላቸውን አካሂደዋል፡፡ የሻቢያ ጦር የሚያደርገውን የስነ-ልቦና ጦርነት ለጦሩ በማስተማር እንዲረጋጋ አድርገዋል፡፡

በናቅፋ የሻቢያ ጦር ባደረሰባቸው ጥቃት የቀኝ እግራቸውን ተመተዋል ሆኖም ይህን በመቋቋም ከጠላት ያስለቀቁት በኩኩባ እና በአፋ ቤት መካከል የሚገኘውን የሻቢያን ደፈጣ የደመሰሱበት ቦታ ተስፋዬ በር ተብሎ ተሰይሟል፡፡ በዚህ ወቅትም የሻለቃነት ማዕረግ አግኝተዋል፡፡ ከናቅፋው ሰብረው ለወጡት መኮንኖች በሙሉ የአንድ እርከን የማዕረግ ዕድገት ሲሰጥ ሻለቃ ከሆኑ በኋላ አምስት ዓመት የሚጠይቀውን የሌተናል ኮሬኔልነት ማዕረግ በአራት ወር አግኝተዋል፡፡

በጥር 1970 ዓ.ም በተደረገ ጦርነት ጭንቅላታቸውን ተመተው ሆስፒታል ገቡ፡፡ ከሆስፒታል ሲወጡ ለመምሪያ መኮንንነት ትምህርት ለመማርና ህክምና ለመከታተል ሶቭየት ህብረት /ሞስኮ/ ፍሩንዜ አካዳሚ ተላኩ፡፡

መስከረም ሁለት ቀን 1972 ዓ.ም የኢትዮጵያ የጦር ሜዳ (ወደር የሌለው) ጀግና ሜዳልያ ባደረጉት ተጋድሎ በጓድ ሊቀመንበር መንግስቱ ኃይለማርያም ተሸለሙ፡፡ የምስክር ወረቀትም ተሰጥቷቸዋል፡፡

ከዚህ በኋላ የቀይ ኮከብ ዘመቻ፣ ዘመቻ ባህረነጋሽ ላይ አዛዥ ሆነው ተሳትፈዋል፡፡ በተጨማሪም በ1983 ዓ.ም መጨረሻ ላይ የቴዎድሮስ ሰራዊት አዛዥ ሆነው አገልግለዋል፡፡ የብርጋዴል ጄኔራልነት ማዕረጋቸውን በ1977 ዓ.ም አግኝተዋል፡፡

## 3.3 ታሪኩ ከግለ-ታሪክ አጻጻፍ መርህ አንጻር

ይህንን ታሪክ ከግለ-ታሪክ አጻጻፍ መርሆች አንጻር ያደረኩትን ፍተሻ እንደሚከተለው አቅርቤአለሁ፡፡

### 3.3.1 ተነባቢነት

አንድ ግለ ታሪክ ተነባቢ ነው የምንለው ግልጽነት፣ ተአማኒነት ካለውና በትክክለኛ መረጃ የተደገፈ ሲሆን ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለአንባቢ ይዞት የመጣው ፋይዳ በአርዓያነቱ የሚማርበት ወይም አዲስ ነገር የሚያሳውቅበት ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ይህንን ሃሳብ በተመለከተ ሳህለሥላሴ ብርሃነማርያም፣ 1992፣ 84/ ሲገልጹ

> የሕይወት ታሪካቸውን የሚጽፉ ሰዎች በእብሪት ተነሳስተው "ታላቅነታቸውን" ለማሳየት ሳይሆን ታላቅ ሥራቸውን ለሌሎች አብነት እንዲሆንና በተለይም ወጣቱ ትውልድ ለታላቅ ስራ እንዲነሳሳ ለማድረግ ነው፡፡ በተጨማሪም ታሪካቸውን በተሟላና በሚያሳምን ሁኔታ ሲያቀርቡት የአንባቢያን አድናቆት እንደሚያተርፉ ሁሉ ባልተሟላና በማያሳምን ሁኔታ ሲያቀርቡ በአንባብያን ዘንድ ቅሬታን ይፈጥራል፡፡

ይህንንም መጽሐፍ ከነዚህ ጉዳዮች አንጻር ስፈትሸው አንባቢ ለአንባቢ ይለያያልና ድፍን አድርጌ የጽሑፉ አቀራረብ አንባቢን ይስባል አይስብም ለማለት ብቸገርም የመጻሐፉን ተነባቢነት በተወሰነ መልኩ አጓድለዋል ያልኳቸውን ነጥቦች ለይቼ ለማሳየት ሞክሬያለሁ፡፡ ለመነበቡም እንቅፋት ናቸው ያልኳቸውን እንደሚከተሉት ከነአስረጅአቸው አስቀምጫለሁ፡፡

- ንባቡ ሲጀምር ያለው "የሐረግ መዘዛ" ፋይዳው ጉልቶ አለመታየቱ፤

አንድ ግለ-ታሪክ በሚዘጋጅበት ጊዜ በውስጡ ስለባለታሪኩ ቤተሰብ፣ ልደት እና ዕድገት፣ የትምህርት ሁኔታ በተወሰነ መልኩ ማሳየት እንደለበት በምዕራፍ ሁለት

ተጠቅሷል፡፡ ይህንንም ሃሳብ በተመለከተ ሳህለስላሴ ብርሃነማርያም፣ /1992፣ 85/ ሲገልጹ

> አጼ ኃይለስላሴ "ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ" በተሰኘው መጽሐፋቸው ስለዘር ሀረጋቸው እንዲህ ይሉናል፤
> "አባቴ ልዑል ራስ መኮንን የታላቁ ሸዋ ንጉስ የሳህለስላሴ ልጅ የልዕልት ተናኜወርቅ ልጅ ናቸው፡፡ አባታቸውም የደባና የመንዝ ባላባት ደጃዝማች ወልደሚካኤል ወልደመለኮት ናቸው፡፡" /ገጽ - 1/

በተጨማሪም፣

> እናታቸውን በሚመለከት የእናታቸውን ስም በመጥቀስ "እናታችን ወ/ሮ የሺመቤት" ከማለት በስተቀር ስለእናታቸው ማንነት አንድም ቃል አይተነፍሱም፡፡ ሌላው ቀርቶ የእናታቸውን አባት ስም ማን እንደሆነ ሳይገልጹልን በዝምታ አልፈውታል፡፡ አጼ ኃይለስላሴን የሚያክል ታላቅ ሰው የወለዱ እናት ማንነታቸው ሳይገለጽ እንዴት ቀረ የሚል ጥያቄ የሚያነሱ አንባቢያን እንዳሉ እርግጠኛ ነኝ፡፡

በማለት ሳህለስላሴ ብርሃነ ማርያም የባለ ታሪኩ እናት ማንነት ባለመገለጹ በእሳቸው እና በአንባቢያን ዘንድ ቅሬታ እንደተፈጠረ ይነግሩናል፡፡

በዚህ መጽሐፍ ውስጥም ከላይ የተገለጸው ጉዳይ ጉልቶ አይታይም፡፡

**አስረጅ፡ 1**

ጸሐፊው ጽሑፋቸውን ሲጀምሩ፤

> በቀድሞ ሸዋ ክፍለ ሀገር፣ ጨቦና ጉራጌ አውራጃ ቸሀ ወረዳ ልዩ ስሙ ሲሰ ተብሎ ከሚጠራው መንደር ከአባቴ ከአቶ ቆትየ/ሃብተማርያም/ ጋና እና ከእናቴ ከወ/ሮ ፈርሸዋት ጋጀወ ተወለድኩ፡፡ ማንበብ እና መጻፍ ስለማይችሉ የትውልድ ዘመኔን ቀንና ዓ.ም. በውል የሚገልጽ ማስረጃ አላገኘሁም፡፡ ከአንዳንድ ታሪካዊ ክስተቶች በመነሳት የተወለድኩው በግምት 1933 ዓ.ም በወርሀ ነሐሴ ሳይሆን አይቀርም ስለሚሉኝ እኔም ት/ቤት ስገባ የትውልድ ዘመኔ ነው ብዬ ያስመዘገብኩት ይኼንኑ ነው፡፡ ለወላጆቼም ከ9 ልጆች መካከል ሦስተኛ ልጅ ነኝ፡፡ /ገጽ - 1/

በማለት ስለራሳቸው የትውልድ ዘመን እና ዓመተምህረት ሲያብራሩ እናትና አባታቸውን ለአንባቢ ስማቸውን ከማሳወቅና ፊደል ያልቆጠሩ መሆናቸውን ከመንገር በስተቀር የሚነግሩት ነገር የለም፡፡ ነገር ግን እናትና አባታቸው ከማን ተወለዱ? የትውልድ ሀገራቸው የት ነው? የሚለውን ጥያቄ ለአንባቢ ጠቁመው ቢያልፉ የተሻለ ይሆን ነበር፡፡

**አስረጅ፡ - 2**

> *ዕድሜዬ ለትምህርት ሲደርስ የዕድሜ መሰሎቼና ጓደኞቼ በአካባቢው በሚገኘው ዘመናዊ ት/ቤት ገብተው ሲማሩ እኔ በአካባቢያችን የቄስ ትምህርት ቤት ስላልነበረ የቄስ ትምህርት ቤት ፍለጋ አክስቴ ዘንድ አክሲል ተወሰድኩ፡፡ /ገጽ - 2/*

*በማለት ይነግሩናል፡፡ ነገር ግን አንባቢ የአክስታቸው ስም ማነው? የአባታቸው እህት ናቸው ወይስ የእናታቸው እህት የሚል ጥያቄ በአእምሮው እንዲጠይቅ አድርገዋል፡፡ ነገር ግን አንድ ግለ ታሪክ ሲዘጋጅ አንባቢ ማግኘት ያለበትን መረጃ መንገር እንጂ በአእምሮው ጥያቄ ትቶ ማለፍ የለበትም፡፡*

- *ከግለ-ታሪኩ ባለቤት ውጪ የሆኑ የተለያዩ ታሪኮች በብዛት ጐልተው መታየታቸው ጽሑፉ ተነባቢነቱን እንዲያጣ ያደርጉታል፡፡ ምክንያቱም አንድ ታሪክ ከአስፈላጊው ርዕሰ ጉዳይ እየወጣ በመጣ ቁጥር አንባቢ ሊሰለች እና ለጽሑፉ ትኩረት ሰጥቶ እንዳያነብ ያደርገዋል፡፡ ይህንንም ሃሳብ በተመለከተ ሳህለስላሴ ብርሃነማርያም፣* /1992፣ 84 — 85/

> *ስለራሱ ሕይወት የሚጽፍ ማንኛውም ሰው ስለመላ ሕይወቱ አንዳችም ነገር ሳያስቀር ሁሉንም ያትታል ማለት አይደለም፡፡ አላስፈላጊ የሆኑ ጥቃቅን ነገሮች ልዘክዝክ ቢል አንባቢው ይሰለች ይሆናል፡፡ ስለራሱ ሕይወት የቱን መያዝና የቱን መጣል እንዳለበት የሚወስነው እሱ ራሱ መሆን አለበት፡፡ ይህን ለማድረግ ሙሉ መብት አለው፡፡ ይሁን እንጂ ይህንን በሚያደርግበት ጊዜ መገለጽ የነበረበትን እውነታ ሳይገልጽ ሲቀር ወይም ያልሆነውን ሆነ ብሎ ቢያቀርብ እውነቱ ገሀድ በሚወጣበት ጊዜ ትዝብት ማትረፉ አይቀርም፡፡ ስለሆነም መነገር የሚገባውን እውነት ለመናገር ድፍረቱ እንዲኖረው ያሻል፡፡ በማለት ይገልጻሉ፡፡*

*አስረጅ፡- ጸሐፊው ከገጽ* 15 - *ገጽ* 21 *ያነሱትን ጉዳይ እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ፡፡*

> *"በአየር ወለድና በኮማንዶ ት/ቤት ሰልጥኜ ስጨርስ በግንቦት ወር* 1956 *ዓ.ም* 3*ኛ ክፍል ጦር ውስጥ* 25*ኛ ሻለቃ ወደሚገኝበት ኦጋዴን ልዩ ስሙ ደገሃቡር የሚባል ቦታ ሄድኩ፡፡"*

*በማለት ከነገሩን በኋላ ስለ ሶማሊያ የድንበር ይገባኛል ጥያቄ ያነሳሉ፡፡ ከዚያም ጦርነቱ መቼ? እና እንዴት? በማን እንደተጠነሰሰ ይነግሩንና በ*1941 *ዓ.ም የፋሺሽት ኢጣልያ መንግስት ሰራዊት በኢትዮጵያ አርበኞችና በእንግሊዝ ድጋፍ ተሸንፎ*

እንደተባረረ፣ ስለ ጣልያን ሰራዊት እና ሌሎች ተዛማጅ ታሪኮችን በስፋት አብራርተው ሲነግሩን ይቆያሉ፡፡

> "ዋናው ጦር ተጠናቆ፤ ሰርጐ ገቦች ወይም የሽምቅ ተዋጊዎች በኦጋዴን አካባቢ በሰፊው መንቀሳቀስ በጀመሩበት ወቅት ነበር ኦጋዴን የደረስኩት ወይም ከጦሩ ጋር የተቀላቀልኩት፡፡" /ገጽ - 21/

በማለት ይገልጻሉ፡፡ ታዲያ እዚህ ጋር ጐልቶ የሚታየው የብ/ጄኔራሉ ታሪክ ሳይሆን በወቅቱ ስለነበረው የጦርነት ድባብ በስፋት የሚያብራራ ነው፡፡ በዚህም የብ/ጄኔራሉ ታሪክ ተደብቆ ይታያል፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው ግለ-ታሪኩን ሲጽፍ የተለያዩ ታሪኮች አይጠቀሱ ማለቴ አይደለም፡፡ እንዲያውም አንድ ሰው ታሪኩን ሲጽፍ ታሪኩ የተከናወነበትን ቦታ ካልጠቀሰ ታሪኩ ወደፊት ሊራመድለት አይችልም፡፡ ይህም ማለት ስለአንድ ሰው ታሪክ ሲጻፍ በተዘዋዋሪ ስለቦታ መነሳቱ አይቀሬ ነው፡፡ በተጨማሪም ስለራስ የተጻፉ መጻሕፍት በአብዛኛው ሲታዩ ስለ ሀገር ጉዳይ ወይም ስለአንድ ቦታ የሚነግሩ ሆነው ቢገኙም ከባለታሪኩ ሕይወት ጐን ለጐን መቅረብ አለባቸው እንጂ በጽሑፉ ውስጥ በስፋት መነገር የለባቸውም፡፡

በተመሳሳይ አጼ ኃይለስላሴ፣ ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ በሚል ርዕስ በ1929 ያሳተሙትን ግለ-ታሪክ ብንመለከት ንጉሱ ከልጅነታቸው ጀምሮ መጽሐፉን ጽፈው ለአንባቢ እስከአበቁበት ወቅት ድረስ ያለውን ታሪካቸውን ከማቅረባቸው ባሻገር በጉልህ የሚታየው ስለማያራምዱት የዘውድ ስርዓት እና ሀገሪቱ በወቅቱ ስለነበረችበት ሁኔታ ነው፡፡

አስረጅ፡ - /ገጽ -30/

> ልጅ እያሱ በድሬዳዋና በሀረር በጅጅጋም ከተሞች እየተመላለሱ አዳሎችን እና ሱማሌዎችን እየሰበሰቡ ሽልማት እየሸለሙ፣ መሳሪያ እየሰጡ በሃይማኖት ወገናችሁ ነኝ እያሉ ሲያሽሟጥጡ ይሰማ ነበር …

**አስረጅ፡- /ገጽ - 129/**

> ኢትዮጵያ አንድነት የሌላት መንግስት ናት እያሉ በዓለም መንግስታት ማህበር ፊት ከሳሾች የሆኑት ኢጣሊያኖች የፕሮፓጋንዳ ሥራ መስራታቸውን መመልከት በጣም ያስደንቃል፡፡ እኛም በትጋት ፕሮፓጋንዳቸውን በማፍረሳችን ያስገርም ነበር፡፡ ነገር ግን ሞከሩ እንጂ ለመለያየት አልቻሉም፡፡

አስረጅ፡ - 3 /ገጽ - 132/

ራስ ጉግሳ ወሌ ከንግስት ዘውዲቱ የተለያዩት ምንም እንኳ በፈቃዳቸው ቢሆን በዚህ በትልቁ የደስታ ዘመን አዲስ አበባ ሳይመጡ … የበጌምድርን ህዝብ በሙሉ ወገን ለማድረግና የጦርነት ኃይል ለማጠናከር ይምክሩ ጀመር።

በተጨማሪም አማኑኤል አብርሃም የሕይወቴ ትዝታ በሚል ርዕስ 1992 አሳትመው ያቀረቡትን ግለ-ታሪክ ስመለከት ከላይ ካነሳሁት ጉዳይ ጋር በተመመሳይ ከራሳቸው ታሪክ ውጪ የሆኑ የተለያዩ ታሪኮች ጉልተው ይታያሉ።

አስረጅ፡ - 1 /ገጽ 117 — 119/

ከመጋቢት 1949 ዓ.ም የዩናይትድስቴትስ ፕሬዚዳንት አይዘንሀወርና የብሪታንያ ጠቅላይ ሚኒስትር ሀሮልድ ማክሚላን፣ የሁለቱንም መንግስታት ጥቅም በሚነኩ ጉዳዮች ላይ ለመነጋገር ከሰሜን አካሜሪ አቅራቢያ በምትገኘው የእንግሊዝ ግዛት በበርሙዳ ደሴት ተገናኙ። . . . ኘሬዚዳንት አይዘንሀወርና ሚስተር ማክሚላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮቻቸውን አስከትለው በበርሙዳ ደሴት ተገናኘተው ለመካከር ወሰኑ።

ሁለቱ የመንግስት መሪዎች ለሦስት ቀናት ከተነጋገሩ በኂላ . . . የተስማሙባቸውን ጉዳዮች በኮሙኒኬ አስታወቁ።

አስረጅ፡ - 2 በምዕራፍ ሁለት፣ ከገጽ 205 — 264 የመካነ እየሱስ ቤተ-ክርስቲያን ምስረታና ጥንካሬ በሚል ርዕስ

በዚያ ዘመን /1947 — 1951/ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ገና በብሄራዊ ደረጃ ባትቋቋምም፣ በ1949 /1957/ ዓ.ም. በዩናይትድስቴትስ፣ ሚኒፖሊስ በተደረገው ሦስተኛ የሉተራውያን የዓለም ፌዴራሲዮን ጉባዔ የአዲስ አበባ መካነ ኢየሱስ ማህበረ ምዕመናን በአባልነት ተመረጡ . . .

እያሉ እስከ ገጽ 264 ድረስ ስለ ቤተክርስቲያን ጉዳይ በስፋት ያትታሉ።

ሌላው ይህ ግለ-ታሪክ ለአንባቢ ይዞት የመጣው ፋይዳ በአርአያነቱ የሚማርበት ወይም አዲስ ነገር የሚያሳውቀው ነው ወይ? የሚለውን ስመለከት ደግሞ ባለታሪኩ ያሳለፉትን የሕይወት ገጠመኝ የጦር ሜዳ ውሎ በሚል ርዕስ ይህንን ጽሑፍ ለአንባቢ ማቅረባቸው ይበል የሚባል ተግባር ቢሆንም ከታሪካቸው ውጪ የተለያዩ ታሪኮችን

በስፋት ማቅረባቸው አንባቢ ከሳቸው ስራ ምን ተምሮአል ወይም አግኝቶአል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ይቸግራል፡፡ ነገር ግን ስለ እሳቸው የሕይወት ታሪክ እና በወቅቱ ስለነበሩ ጦርነቶች ምንም ዓይነት ዕውቀት የሌለውን አንባቢ በተወሰነ መልኩ ግንዛቤ አስጨውበታል የሚል እምነት ቢኖረኝም ባለታሪኩ ታሪካቸውን ሲያቀርቡ ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ታሪኮች (ለምሳሌ ስለሕይወት ያላቸውን አመለካከት፣ ያጋጠሟቸውን አሳዛኝና አስደሳች ነገሮች፣ በሕይወት ዘመናቸው ያከናወኗቸውን ዋና ዋና ተግባራት) ከታሪካቸው ጐን ለጐን ቢያቀርቡ አንባቢ ከእሳቸው ብዙ ሊማርና ሊገነዘብ ይችል ነበር፡፡

ከላይ ለጽሑፉ መነበብ እንቅፋት ያልኳቸውን ነገሮች ስጠቅስ መጽሐፉ ጭራሽ ተነባቢ አይደለም ማለቴ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በታሪኩ ውስጥ ለመነበብ እንቅፋት የሆኑ ነገሮች እንደመኖራቸው አንባቢን እንዲያነብ የሚገፋፉ ጉዳዮችም አልፎ አልፎ አልታጡም፡፡ ለምሳሌ ያህል በየጽሑፉ መሐል በራሳቸው አጻጻፍ ስልት የጻፉአቸውን አንዳንድ ቃላት በጽሑፋቸው ግርጌ ማብራሪያ ሰተውበት ይገኛል፡፡

**አስረጅ፡- 1 /ገጽ - 88/**

> አፈጻጸም፡- የአየር ወለድ ግዳጅ ይበልጥ ስኬታማ ለማድረግ አንድ ፋና ወጊ የአየር ወለድ አባል ከሄሊኮፕተር ከቀ. ቀን መቀነስ አንድ በሠ-ሰዓት ይዘላል፡፡ . . .

በማለት የገለጹትን በስተግርጌ ደግሞ እንዲህ ብለው አስቀምጠውታል፡፡

> .ቀ. ቀን ውጊያ የሚጀመርበት ወቅት ሲሆን
> .ሠ - ሰዓት ደግሞ ውጊያ የሚጀመርበት ሰዓት ነው፡፡ /ገጽ - 88/

አስረጅ፡ - 2 /ገጽ - 22/

> ጠላት ደፈጣ ውስጥ በድንገት እንደገባ አብሪዎች በማውጣት አካባቢያችንን እየተቆጣጠርን መሄድ እንደለብን፣ በጉዞ ላይ ርቀት . . . እያንዳንዱ ሰው መዘጋጀት እንዳለበት ትዕዛዝ ሰጡ፡፡

በማለት በጽሑፋቸው የገለጹትን ሃሳብ በጽሑፉ ግርጌ

- አብሪ ማለት በዋናው ጦር ላይ ድንገተኛ አደጋ እንዳይደርስ ከዋናው ጦር ከ50 — 100 ሜትር ርቀት በመሄድ ስለጠላት ሁኔታ እየሰለሉ ለዋናው ጦር መረጃ የሚያቀበሉ አነስተኛ ቡድን (የሚያነቁ) ማለት ነው፡፡

### 3.3.2 የመረጃ አቀራረብ

አንድ ግለ ታሪክ በሚዘጋጅበት ጊዜ ከታሪኩ ጐን ለጐን የተለያዩ መረጃዎች አብረው እንደሚቀርቡ በምዕራፍ ሁለት ተነስቷል፡፡ እነዚህ መረጃዎች የምንላቸው ፎቶ ግራፎች፣ የምስክር ወረቀቶች፣ ካርታዎች፣ ስዕሎች፣ ግራፎች የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ከዚህም በመነሳት ጸሐፊው ግለ-ታሪካቸውን ሲጽፉ ቀዳማይ እና ካዕላይ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅመዋልን? የሚለውን ስመለከት አንድም ዋቢ ራሴ በሚል ቀዳማይ መረጃ እንዲሁም የተለያዩ ድርጊቶች ሲፈጸሙ፣ ለየት ያሉ ክስተቶች ሲከሰቱና ማስታወሻ ያሉትን ሰነዶች፣ ፎቶግራፎች፣ ካርታዎች፣ በአባሪነት ካዕላይ አድርገው አቅርበዋል፡፡

**አስረጅ፡**

- በ1956 ዓ.ም ሀረር ከተማ ከሀረር ጦር አካዳሚ በም/፲/ አለቅነት ማዕረግ ሲመረቁ ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ጋር ለመታሰቢያነት የተነሱት ፎቶ ግራፍ /ገጽ - 15/
- በ1972 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሰራዊት ውስጥ የመጨረሻ ከፍተኛ የሆነውን የህብረተሰባዊ ኢትዮጵያ ጀግና ሜዳይ ፕሬዚዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም ሲሸልሟቸው የሚያሳይ ፎቶግራፍ /ገጽ - 225/
- በ1979 ዓ.ም. ከ10 ዓመት በኂላ በኰኰብ እና በአፋ ቤት መሃከል የሚገኘውን የሻቢያን ደፈጣ ደምስሰው የወጡበትን ማነቆ የተስፋዬ በር ተብሎ በወገንና በጠላት በተሰየመው ቦታ የተነሱት ፎቶግራፍ /ገጽ - 185/
- በተለያዩ ጊዜያት በስልጠና እና በስራ ላይ ሆነው የተነሱአቸው የተለያዩ ፎቶግራፎች /ገጽ 232፣251፣256፣276/
- በተለያዩ ጊዜያት ያገኙአቸው ዝርዝር ማዕረጐች ከነዓመተምህረታቸው /ገጽ - 321/
- የተሰጡአቸው የምስጋና ደብዳቤዎች ዝርዝር ከነዓመተምህረታቸው /ገጽ - 323፣313፣290፣291፣257/
- የሰሩባቸውን ቦታዎች እና የነበራቸውን ኃላፊነት የሚያሳዩ መረጃዎች /ገጽ - 320/
- የተካፈሉባቸው የጦርሜዳዎች /ገጽ - 32/

- በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የተማሯቸው ትምህርቶች /ገጽ - 319፣ 313፣ 290 — 291፣257/
- በጦርነቱ ጉዳት በደረሰባቸው ሰዎች በሚመለከት የተሰጠ መረጃ /ገጽ 251/
- የሐረር ዙሪያ መከላከል እና መልሶ ማጥቃት የሚያሳይ ካርታ /ገጽ 197/

እንደአስፈላጊነታቸው በየጽሑፋቸው መሐል እና በጽሑፋቸው መጨረሻ ላይ አባሪ ሆነው ቀርበዋል፡፡ በዚህም የጸሐፊውን የመረጃ አቀራረብ ይህ ይጐላቸዋል ብዬ ለማለት ባልደፍርም ታሪኩ የረጅም ጊዜ እንደመሆኑ መጠን መረጃዎቹ ከዚህ በበለጠ ተጠናቅረው ቢቀርቡ የታሪኩን ተአማኒነት ያጐላሉ የሚል አስተሳሰብ አለኝ፡፡

## 3.3.3 ትክክለኛነት (እውነተኛነት)

አንድ ግለ-ታሪክ ትክክለኛ /እውነተኛ/ ነው የምንለው በትልምና በመቼት ታሪኩን በቅደም ተከተል አብራርቶ ሲነግረን ነው፡፡ ትልም በአንድ ታሪክ ውስጥ የምክንያትና የውጤት ትስስር ሲሆን፣ መቼት ደግሞ ባለታሪኩ ታሪኩን ለአንባቢ ሲያቀርብ መቼና የት እንዳከናወነው የሚዘረዝርበትን የጊዜ ክልል የሚያሳውቅበት ነው፡፡

ግለ-ታሪኩ በትልም፣ በመቼት እውነተኛና ትክክለኛ ነው ወይ? የሚለውን ከመመልከቴ በፊት ግለ-ታሪክን በተመለከተ የስኬት እና የክስረት ጉዳይ የቅርብ ሰው ተነስቶ ወይም ከዚህ ቀድሞ በበባለታሪኩ ላይ የተጻፈ ነገር ካልተገኘ በስተቀር ታሪክ ጸሐፊው እኔ እራሴ እያለ የጻፈው መረጃው ነውና እውነተኛ ታሪክ ይሁን ወይም የተዛባ የግል አመለካከት ይራመድበት ለማወቅ ይቸግራልና አምነን ልንቀበለው የግድ ነው፡፡ ምክንያቱም ግለ-ታሪክ በባለ ታሪኩ ባለቤት የሚጻፍ የጹሑፍ ክፍል ስለሆነ ራስን ከፍ ከፍ የማድረግ፣ ከተጠያቂነት የመሸሽ፣ ራስን ለመተቸት አለመድፈር ጐልተው ይታያሉ፡፡ ነገር ግን መመዘኛው ለዚህ መጽሐፍ አስቸጋሪ ነው ብዬ ለማለፍ ግን አልወዳድኩም፡፡ ከትልምም ሆነ ከመቼት አንጻር ለአእምሮዬ የተአማኒነት ጥያቄ የጫሩብኝን ጉዳዮች ከነ አስረጂአቸው አቀርባለሁ፡፡

የትልም (ምክንያት እና ውጤት ጣጣ) እውነተኛና ትክክለኛነት በተመለከተ ደራሲው በግለ ታሪካቸው ውስጥ የልጅነት ሕይወታቸው ላይ ከእናታቸው እና ከአባታቸው ጋር እንደሚኖሩና እናታቸው የተለየ እንክብካቤ እያደረጉ እንዳሳደጉአቸው ይነግሩን እና ቀጥለው ለትምህርት አካባቢያቸውን ለቀው ሄደው እንደተማሩና በጥሩ

ውጤት በማለፋቸው አለማያ ኮሌጅ ገብተው እንዲማሩ ዕድል እንደገጠማቸው ከነገሩን በኋላ የምዝገባው ወቅት እስኪደርስ ወደ ትውልድ ቦታቸው ሲሄዱ አባታቸው በጸና ታመው ከታናሽ እህታቸው ጋር ብቻ እንዳገኙአቸው ይነግሩናል፡፡ እዚህ ላይ ስለ እናታቸው የተጠቀሰ ጉዳይ የለም፡፡ ለትምህርት ወደ ሌላ ሀገር ሊሄዱ በሚነሱበት ጊዜ ደግሞ እናታቸው እንዳሉ ነግረውን ሲመለሱ ግን ስለ አባታቸው ጉዳይ ብቻ ሲያነሱ ይታያል፡፡

ከላይ የተነሳው ጉዳይ ታዲያ ጸሐፊውን ለግምት ይዳርጋል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ስለሆነም ግለ-ታሪክ ኢ-ልቦለዳዊ የስነጽሑፍ ዘርፍ ስለሆነ ልክ እንደፈጠራ ሥራ ለአንባቢ የቤት ስራ መስጠት የለበትም፡፡ ይህም ማለት አንባቢ ከታሪኩ ትክክለኛውን መረጃ በቀጥታ ማግኘት አለበት ለማለት ፈልጌ ነው፡፡

በአጠቃላይ ደራሲው በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በርካታ እና ጥቃቅን የሚባሉ ጉዳዮችን ጽፈው እድናነብ ካደረጉን በኋላ ይህንን ጉዳይ አለመጻፋቸው ለትምህርታቸው መደናቀፍ ምክንያት አይደለም ብለው ይሆን? የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ በዚህም የምክንያት እና የውጤት መድበስበስ መኖሩን እንመለከታለን፡፡

አስረጅ፡ - ከገጽ /3 — 4/

> እናቴ ከስቼ እከክ ወሮኝ ስታየኝ ለቅሶዋን አቀለጠችው፡፡ እንባዋ እርግፍ እርግፍ አለ፡፡ የእናቴን ጩኸት የሰሙ ጐረቤቶቻችን እና ዘመድ አዝማድ ተሰብስበው እያዩኝ እነሱም ማልቀስ ጀመሩ፡፡
>
> እናቴ ሁለተኛ ት/ቤት የሚባል ቦታ ልጄ በፍጹም ድርሽ አይልም ሞቻታለሁ በማለት አባቴ በሌለበት ፎከረች፡፡ ቶሎ ብላ ውሃ አሙቃ ሰውነቴን አጥባ ቅቤ ቀባችኝ፡፡
>
> እንደተለመደው ላሞች ሲታለቡ ትኩስ ወተት ላይ ቅቤ ጨምራ አጠጣችኝ፡፡

በማለት እናታቸው የሚያደርጉላቸውን እንክብካቤ ይነግሩን እና የእናታቸውን ጉዳይ በጭራሽ በመተው አንባቢ እናታቸውስ? ወዴት ሄዱ? ተፋቱ? ሞቱ? የሚለውን ጥያቄ እንደጠይቅ አድርገው በጽሑፋቸው ግርጌ "በዚያን ጊዜ እናትና አባቴ ተለያይተው (ተፋትተው) እናቴ ሌላ ባል አግብታ ትኖር ነበር፡፡" በማለት ይገልጻሉ፡፡

አስረጅ፡ - 1

በ1953 ዓ.ም የትምህርት ዘመን አለማያ ኮሌጅ ገብቼ እንድማር ኮሌጁ የተቀበለኝ ለመሆኑ ከዲኑ የተጻፈ ደብዳቤ ደረሰኝ፡፡ በቅድሚያ ግን በነሀሴው ወር አጋማሽ ላይ 1953 ዓ.ም ኮሌጅ ገብቼ ትምህርቴን የምቀጥል መሆኔን አዲስ አበባ እርሻ ሚኒስቴር ቅጥር ግቢ ውስጥ በአካል ተገኝቼ ማረጋገጥ እንዳለብኝ ደብዳቤው ላይ ተጽፎ ነበር፡፡ በክረምት ትምህርት ሲዘጋ አዲስ አበባ መቆያ ቦታ ስለሌለኝ ወደ ትውልድ መንደሬ ነበር ያመራሁት፡፡ እዚያ ስደርስ ወላጅ አባቴ በጣም ታሞ አገኘሁት፡፡ አባቴ አጠገብ የነበረችው ትንሽ እህቴ ብቻ ነበረች፡፡ አባታችን ራሱን ችሎ መቀመጥ አይችልም፣ ምግብ የሚመገበውና ውሃ የሚጠጣው በሰው እርዳታ ነው፡፡ ለሶስት ወራት እኔና እህቴ እየተረዳዳን ስናስታምመው ቆየን፡፡ በአባቴ ህመም ምክንያት በነሀሴ ወር 1952 ዓ.ም አዲስ አበባ እርሻ ሚኒስቴር በተባለው ቀን ቀርቤ ቃለ መጠይቁን መውሰድ አልቻልኩም፡፡ /ገጽ 8/

ሌላው ባለ ታሪኩ ለታሪካቸው መቀጠል ምክንያት ይሆናል ብለው አስበው ይሁን ሌላ አንድን ነገር ሊነግሩን ሲፈልጉ የተለያዩ ከታሪኩ ጋር ተያያዥነት የሌላቸውን ነገሮች በየጽሑፋቸው መሐከል በማስገባታቸው የምክንያትና የውጤት መድበስበስ እንዲፈጠር አድርገዋል፡፡

አስረጅ፡ - 1 /ገጽ 168 — 171/

አመራር ሰጪዎች የሚያስከትለውን ችግር እና የሚያስነሳው አመጽ ስለምንረዳ ደፍረን ተው ማለት አልቻልንም፡፡ የጦሩ በቡድን ሆኖ መወያየት በቀጣይነት የጦሩ ጠንክሮ የመታገል መንፈስ እንደሚሸረሽረውና ተጽዕኖ እንደሚያደርግ እንገምታለን፡፡

ባገኙት አጋጣሚ ተሰብስባችሁ አትወያዩ ማለት ደግሞ ተፈጻሚነት ስለማይኖረው አይተን እንዳላየን ማለፍ ብቻ ነው የመረጥነው፡፡

*እስሚመሽ ጠብቆ ጭለማን ከለላ አድርጎ እንደተለመደው ከምሽግ ምሽግ እየተዘዋወርኩ ፕሮፓጋንዳውን በፀረ-ፕሮፖጋንዳ ለማክሸፍ ጥረቱን ቀጠልኩ፡፡ "እረ ለመሆኑ ሻቢያ ለአምስት ተከታታይ ወራት ያለማቋረጥ የተለያዩ ስልቶችን እየተጠቀመ የናቅፋን ጦር ለመደምሰስ ያላደረገው ጥረት ምን አለ? ታዲያ ዛሬ ልምጥምጡን ምን አመጣው? በቆራጥነትና በጀግንነት ማጥቃቱን ተከላክለን*

*አሳፍረን ስለመለስነው፤ አይደለም? ዓላማውን ከግብ ለማድረስ አይደለም? አሁን ደግሞ የማጥቃቱ ስልት ውጤት አልሰጥ ሲለው ዓላማውን ከግብ ለማድረስ፤ በስነ ልቦና ጦርነት ሬቱን ማር፣ ድንጋዩን ዳቦ፣ ነጩን ጥቁር ነው እያለ ለማሳመን እየሞከረ ነው። . . .*

*ናቅፋ በዓለም አቀፍ ፕሬስና መገናኛ ብዙሃን ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው፤ ብዙ የተባለለትና ታዋቂነት ያገኘ የጦር አውድማ ነው። ሻቢያ በዓለም ህብረተሰብ ዘንድ ታዋቂነትና ድጋፍ በማግኘት ናቅፋን በቁጥጥር ሥር ለማድረግ የማይፈነቅለው ድንጋይ አይኖርም።*

*ተኩስ አቁመን እንደራደር ማለቱ ማንን ለመጥቀም ነው? እኛን ለመጥቀም እንዳልሆነ እንገነዘባለን። የዚህ ዓይነቱ የማታለያና የማግባቢያ ፈሊጥ አይገነዘቡም ብሎ መገመቱ የሻቢያን ማንነት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። . . .*

በማለት የስነልቦናውን ጦርነት እንደተለመደው ማታ ማታ ከምሽግ ምሽግ እየተዘዋወርኩ ለማርገብ ጦሩን ለማረጋጋት ሞከርኩ።

ከላይ እንደተገለጸው ባለታሪኩ ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ለታሪካቸው የምክንያት ውጤት መድበስበስ ቢፈጥሩም በአጠቃላይ ሲታይ ግን ታሪካቸውን በምክንያት እና ውጤት በማስተሳሰር ለአንባቢ ግልጽ አድርገው ለማቅረብ ሞክረዋል። ለምሳሌ ያህል ባለታሪኩ የልጅነት ሕይወታቸውን ሲገልጹ እና በአካባቢያቸው ትምህርት ቤት አለመኖሩን በቅደም ተከተል ማስቀመጣቸውን እንደ ጥንካሬ ተመልክቼዋለሁ።

**አስረጅ፡ - ከገጽ /1 — 2/**

እንደማንኛውም የገጠር ልጅ በተወለድኩበት መንደር ከዕድሜ መሰሎቼ ጋር ውሃ ተራጭቼ፣ ጭቃ አቡኩቼ፣ ትግል ታግዬ፣ ሌጣ በቅሎ ተቀምጬ፣ በወራጅ ወንዝ ዋኝቼ ነው ያደኩት።

ወላጆቼ በአካባቢው ንብረት አላቸው ከሚባሉት ተርታ ይቆጠሩ ስለነበረ ቶሎ ቶሎ እንዳድግላቸው ትኩስ ወተት ከነአረፋው፣ አንዳንድ ጊዜ ቅቤ ተጨምሮበት ከአቅሜ በላይ ይግቱኝ ነበር።

ፋሺሽት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረበት ዘመን ዓላማው ግዛቱን ማስፋፋት ብቻ ሳይሆን ባህሉንና ሀይማኖቱንም ጭምር የማስፋፋት ተልእኮ ስለነበረው፣ በቸሀ ወረዳ እምድብር ከተማ የካቶሊክ ቤተክርስትያን አሰርቶ

የአካባቢውን ነዋሪዎች የዕምነቱ ተከታይ እንዲሆኑ ከፍተኛ ጥረት ያደርግ ነበር፡፡ ስለዘመናዊ ትምህርት ጠቀሜታ ለአካባቢው ነዋሪ ህዝብ ግንዛቤ በማስጨበጥ ልጆቻቸውን እንዲያስተምሩበት አንድ ዘመናዊ ት/ቤት ቤተክርስትያኑ አጠገብ አሰርቶ ሕጻናትን በማሰባሰብ ያስተምር ነበር፡፡ . . .

ዕድሜዬ ለትምህርት ሲደርስ የዕድሜ መሰሎቼና ጓደኞቼ በአካባቢ በሚገኘው ዘመናዊ ት/ቤት ገብተው ሲማሩ እኔ በአካባቢያችን የቄስ ት/ቤት ስላልነበረ የቄስ ት/ቤት ፍለጋ አክስቴ ዘንድ አክሊል ተወሰድኩ፡፡

መቼትን በተመለከተ ደራሲው በጦርነት ዓለም ያከናወኑት ሥራ በርካታ እንደሆነ እና ከ1953 — 1983 ዓ.ም ድረስ በሰራዊቱ ውስጥ ማገልገላቸውን ስመለከት የሰሩትን ሥራ በዓመተምህረት እና የሰሩበትን ቦታ በመጥቀስ ለተደራሲያቸው ሙሉ መረጃ አስተላልፈዋል የሚል ዕምነት አለኝ፡፡ ይህም ማለት ባለታሪኩ ለ30 ዓመታት የሰሩአቸውን ሥራዎች እና የሰሩባቸውን ቦታዎች አጣጥመው አቅርበዋል፡፡

አስረጅ፡ - በምዕራፍ 7 በገጽ 64 ላይ "የ1966 ዓ.ም ህዝባዊ አብዮት ሰራዊት" በሚል ንዑስ ርዕስ ውስጥ እንዲህ በማለት ያቀርባሉ፡፡

> በአጼ ኃይለስላሴ ዘመነመንግስት ጊዜ የነበሩ የምክትል ጦር፣ የአየር ኃይል፣ የባህርኃይል እና ልዩ ልዩ ክፍሎች እንደ አየር ወለድ፣ መድፈኛና ታንከኛ የመሳሰሉት የራሳቸው የሆነ ልዩ ልብስ፣ መለዮና አርማ ነበራቸው፡፡ . . .

እያሉ በዝርዝር ሲነግሩን ይቆዩና፤

> ከአውሮፕላን ዘለን 15ኛ ሻለቃን ለማጠናከር እንድንችል ፍቃድ አንጠይቅም? ተባባልን … በሚቀጥለው ቀን ቅድመ ዝላይ ዝግጅት ለማድረግ ከመንደፈራ በሄሊኮፕተር አስመራ ገባን፡፡ /ገጽ 75/

በማለት ታሪኩን በጊዜ ቅደሞ ተከተል በዝርዝር አስቀምጠውታል፡፡ ስለሆነም 1966 ዓ.ም የደርግ አገዛዝ ዘመን መሆኑን እና በወቅቱም በአስመራ እና በአካባቢው አለመረጋጋት መኖሩን ገልጸዋል፡፡ ይህም በታሪክ የታወቀ በመሆኑ የመቼቱ ጉዳይ ትክክለኛነቱ አጠራጣሪ አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ እንድደርስ አድርጐኛል፡፡

በአጠቃላይ ይህን ግለታሪክ ከትክክለኛነት (እውነተኛነት) አንፃር ሳየው ጸሐፊው ታሪካቸውን በተለያዩ መረጃዎች በማስደገፍ እና ማብራሪያ የሚያስፈልጉአቸውን ጉዳዮች አብራርተው ለማስቀመጥ ከመሞከራቸው ባሻገር ከታሪካቸው ጐን ለጐን ለታሪኩ

ትክክለኛነት ያግዙኛል ያሏቸውን የተለያዩ ንዑሳን ታሪኮች የተፈጸሙባቸውን ቦታዎች እና ዓመተምህረቶች በጊዜ ቅደም ተከተል እና በምክንያትና ውጤት በማስተሳሰር በዝርዝር አቅርበው ጽሑፋቸው በአንባቢ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ የራሳቸውን ጥረት ሲያደርጉ ይታያል፡፡ ነገር ግን ለጽሑፋቸው ትክክለኛነት ብለው ያቀረቡዋቸውን ታሪኮች በስፋት ከመዘርዘር ይልቅ እንደ አስፈላጊነታቸው ሳይበዙ ከራሳቸው ታሪክ ጐን ለጐን አብረው ቢያቀርቡዋቸው በተሻለ ለታሪኩ ትክክለኛነት ያግዛሉ ብዬ አምናለሁ፡፡

### 3.3.4 ተአማኒነት

አንድ ግለ-ታሪክ ተአማኒ ነው የምንለው ጸሐፊው ታሪኩን በተለያዩ መረጃዎች አስደግፎ ከተጻፈበት ጊዜ ጋር አጣጥሞ ሲያቀርብ ነው፡፡

ግለታሪኩ በፎቶግራፍ፣ በፎቶ ኮፒ፣ በልዩ ልዩ ሰነዶች የተደገፈ ነወይ? የሚለውን ስመለከት ለማየት የፈለግኩት መረጃዎቹ ከዘመኑ ጋር ሲታሰቡ ተአማኒ ናቸው ወይ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እንጂ ታሪኩ በፎቶግራፍ፣ በፎቶ ኮፒ፣ በልዩልዩ ሰነዶች ስለመደገፋ በመመዘኛ 3.3.2 ስር ያየሁት ስለሆነ አልደግመውም፡፡ ፎቶግራፉን በተመለከተ በቁጥር አነስተኛ ከመሆናቸው ባሻገር የተወሰኑት የተአማኒነት ጥያቄ ጭረውብኛል፡፡ ምክንያቱም ፎቶ ግራፎቹ እና በግርጌ የተቀመጡትን ጽሑፎች ተጣጥመው አላገኘኋቸውም፡፡

አስረጅ፡- በገጽ 267 የቀረበውን ፎቶ ግራፍ ስመለከት በግርጌው "በመከላከያ ሚኒስቴሩ ለተመራ ከፍተኛ ቡድን ወደፊት የአየር ወለድ ክፍለ ጦር ጠቅላይ ሰፈር እንዲሆን ስለተመረጠው ቦታ ገለጻ ሲደረግ" በማለት ይነግሩናል፡፡ ነገር ግን ፎቶ ግራፉን መቼ እንደተነሱት የሚገልጽ መረጃ ስለሌለ ይህን መረጃ ከተአማኒነት አንጻር ስፈትሸው አጠራጣሪ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

ሌላው በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ገጽ ላይ የቀረቡትን ፎቶ ግራፎች ስመለከት በግርጌው "1971 ዓ.ም. ከአስመራ ምሽግ ሰበራ እስከ መሳሊት ግንባር ድረስ የነበረውን ውጊያ ከመሩ መኮንኖች ጥቂቶቹ መሳሊት አካባቢ ቁጥር 1 እና 2" በማለት ገልጸዋል፡፡ በዚህም ፎቶግራፉን የተነሱበትን ዓመተምህረት መጠቆማቸው የታሪኩን ተአማኒነት አጉልቶታል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ምክንያቱም "የአስመራ ዙሪያ ምሽግ መስበር" በሚል ንዑስ ርዕስ የቀረበው ታሪክ በ1971 መከናወኑ በጽሑፉ ተገልጿልና፡፡

አስረጅ፡- /ገጽ - 237/

. . ኪነቱ ሲጠናቀቅ የኤርትራ ጦርነት እንዲያስተባብር የተቋቋመው ኮሚቴ አስመራ ዙሪያ ስላለው አዛዥ መኮንኖች ሰብስበን ህዳር 11/1971 ዓ.ም. በሁሉም ግንባር የጦሩ አሰላለፍ እንዴት እንደሆነ፣ የማጥቂያ አቅጣጫዎች በየት በየት በኩል እንዲሆን እንደተወሰነ፣ አዝማቾች እነማን እንደሆኑ እንደሚከተለው ገለጽን።

በፎቶኮፒ እና በተለያዩ ሰነዶች የቀረበውን መረጃ በተመለከት ከፎቶግራፎቹ በተሻለ ግልጽና ተአማኒ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ። ምክንያቱም ባለታሪኩ ያገኙአቸውን ሹመቶች እና ሽልማቶች፣ የሰሩባቸውን እና የተማሩባቸውን ቦታዎች በሚገባ የሚገልጹ ስለሆኑ ነው።

**አስረጅ፡ - 1 /ገጽ 62/**

ከበረራ ደህንነት ሥራ ብሰናበትም የስልጠናው ሥራ ሰልጣኞች ድሬድዋ ድረስ እየተላኩ እስከ 1967 ዓ.ም ድረስ ሳሰለጥን ቆይቻለሁ።

የበረራ ደህንነት ሰራተኞችን በማሰልጠን ለአደረግሁት አስተዋጽኦ ከበረራ ደህንነት አዛዥ ከሻለቃ ካሳ ገ/ማርያም የምስጋና ደብዳቤ ተጽፎልኛል።

ብለው የተሰጣቸውን የምስጋና ደብዳቤ ፎቶ ኮፒ አብረው አያይዘዋል።

**አስረጅ፡ - 2 ገጽ /312 — 314/**

ህዳር 25/1978 ዓ.ም ከሜ/ጄ መርዕድ ንጉሴ የባህረ ነጋሽ ምዕራፍ ሦስት ዘመቻ ባደረኩት አስተዋጽኦ የምስጋና ደብዳቤ ተጻፈልኝ። ደብዳቤውም እንደሚከተለው ይነበባል።

በማለት የተሰጣቸውን ደብዳቤ ፎቶ ኮፒ አያይዘው አቅርበዋል።

በተጨማሪም የተካፈሉባቸውን የጦር ሜዳዎች ከነ ዓመተምህረታቸው በቅደም ተከተል እንደሚከተለው አስቀምጠዋል።

**አስረጅ፡- /ገጽ -321/**

የተካፈልኩባቸው የጦር ሜዳዎች

- በ1969 ዓ.ም. ኤርትራ ናቅፋ 15ኛ ሻለቃን ከሻቢያ ከበባ ለማላቀቅ በተደረገ ውጊያ
- በ1970 ዓ.ም በኢትዮ ሶማሊያ ጦርነት ምሥራቅ ኢትዮጵያ
- በ1971 ዓ.ም ኤርትራ የአስመራ ዙሪያ ምሽግ ሰበራ በኤላቦርድና በመስሊት ውጊያ

- በ1976 ዓ.ም ኤርትራ ከአረዛ - ሙልቂ - በሾቃ - ውጊያ
- በ1977 – 1979 ዓ.ም ኤርትራ
- በ1977ዓ.ም. - በባሬንቱ መልሶ ማጥቃት ውጊያ
- በ1978 ዓ.ም - በዘመቻ ባህረ ነጋሽ በባሬንቱ ግንባር
  - በናቅፋ - ግንባር መልሶ ማጥቃት
- በ1978 ዓ.ም በዘመቻ ባህረ ነጋሽ በአልጌና - ግንባር
  - በሃልሃል - ግንባር
  - በዘመቻ - ቀይባህር
  - ከምጽዋ - ዜይላ ግንባር

በአጠቃላይ ይህ ግለ-ታሪክ ከተአማኒነት አንጻር ሲጤን የፎቶ ግራፉ ጥራት ማነስና በትክክለኛ መረጃ ተደግፎ አለመቀመጥ እንደሚጕድሉትና በሌላ በኩል ደግሞ በፎቶ ኮፒ እና በተለያዩ ሰነዶች የተቀመጡት መረጃዎች በጥሩ ሁኔ ታ እንደተንጸባረቁበት ይታያል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# ማጠቃለያና ጥቆማ

## 4.1 ማጠቃለያ

“የጦር ሜዳ ውሎ” የተሰኘው መጽሐፍ በብርጋዴል ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተማርያም በ1997 የተጻፈ ሲሆን ታሪኩ የሚያጠነጥነው ባለታሪኩ ከ1953 — 1983 ዓ.ም ድረስ በተለያዩ የጦርነት ቦታዎች መሳተፋቸውንና በወቅቱ የነበሩትን የጦርነት ድባቦች ለአንባቢ የሚያሳይ ታሪክ ነው፡፡ በተጨማሪም ባለታሪኩ የተካፈሉባቸው የጦር ሜዳ ቦታዎች የሰሯቸው ሥራዎችና ያገኞቸው ሹመቶችና ሽልማቶች በታሪኩ ውስጥ ተካተው ይገኛሉ፡፡

የዚህ ጥናት ዓይነተኛ ዓላማም ታሪኩ ተነባቢነቱ ምን ያህል እንደሆነ መለየት፣ የመረጃ አቀራረቡ አግባብነት መመርመር፣ ትክክለኛነቱን (እውነተኛነቱን) በመስኩ መርህ መሰረት መግለጽና ተአማኒነቱን ፈትሾ ማመልከት ነው፡፡

ተነባቢነትን ከገጽ 16 – 21 እንደገለጽኩት ግልጽነት፣ ተአማኒነትና ትክክለኛ መረጃን ተደግፎ የቀረበ ሲሆን ነው፡፡ በተጨማሪም ፋይዳ ያለው ሲሆን አንባቢ

- በአርአያነቱ የሚማርበት
- አዲስነገር የሚያውቅበትና
- በተሟላና በሚያሳምን አኳኋን የቀረበ ሲሆን ነው፡፡

እነዚህን ጉዳዮች ተመርኩዤ የሚከተሉትን አሉታዊና አዎንታዊ ጉኖች በፍተሻዬ አግኝቻለሁ፡፡

በአሉታዊ (በድክመት) መልኩ የፈረጅኳቸው የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ስማቸውን ብቻ ሳይሆን የቤተሰባቸውን ዳራም በአጭሩ አልጠቀሙም፡፡ ገጽ 17
- መጽሐፉ ገጽ 2 ላይ አክስታቸው ዘንድ ለትምህርት መወሰዳቸውን ተናግረዋል፡፡ ነገር ግን የአባታቸው እህት ወይም የእናታቸው እህት መሆናቸውን አልገለጹም፡፡ በተጨማሪም ስማቸውንም አልጠቀሱም፡፡
- ከገጽ 15 – 21 ላይ ስለራሳቸው ታሪክ ሳይሆን ስለሶማሊያ ጦርነት በሰፊው አትተዋል፡፡ እነዚህ ተነባቢነትን አሉታዊ በሆነ መልኩ በተወሰነ መጠን የሚነኩ መሆናቸውን ደርሼበታለሁ፡፡

በአዎንታዊ (በጥንካሬ) ገጽታ ያየኋቸው ደግሞ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ግለ-ታሪኩ በአርዓያነት ረገድ ባለታሪኩ በውትድርና መስክ ለረጅም ዓመታት በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች በትጋትና በቆራጥነት ሰራዊቱን ማገልገላቸውና በቆራጥ ዓላማ፣ በድፍረትና በጽናት በመስኩ ባገኙትም እድገት ጥሩ ምሳሌ ሆነው መገኘታቸው፤
- ለአንዳንድ እንግዳ ቅንብሮች 'ቀ. ቀን' ፣ 'ሠ . ሰዓት' ለመሳሰሉት በግርጌ ማስታወሻ ማብራሪያ መስጠታቸው ለተነባቢነት እገዛ አለው፡፡

የመረጃ አቀራረብን በተመለከተ ከገጽ 22 – 23 እንዳስቀመጥኩት ከታሪኩ ጋር የሚሔዱ ልዩ ልዩ መረጃዎችን ይመለከታል፣ በታሪኩ ውስጥ የተነሱ ሀቆችን የሚያሳይ ሕያው የሚያደርግ ነባራዊ ሰነድ ነው፣ ታሪኩን ሕያው ጠንካራና አሳማኝ ያደርገዋል፡፡ በተጨማሪም መረጃው መኖር ብቻ ሳይሆን አግባብነት ያለውና የሚፈለገውን ያህል ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡

ይህ ግለ-ታሪክ በመረጃ ዓይነት (Variety) ብዛትና ጥርቅም በጥሩ ሁኔታ ላይ እንዳለ ለማየት ችያለሁ፡፡ ምክንያቱም በጥናቴ ገጽ 22 – 23 እንዳሳየሁት

- ቁልፍ ክንዋኔዎችን የሚያሳዩ ፎቶግራፎች፣
- በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የተከታተሏቸውን ሥልጠናዎች የሚያሳዩ ፎቶግራፎች፣
- የምስጋና ደብዳቤዎች፣
- በኃላፊነት የሰሩባቸውን ቦታዎች የሚያሳዩ ዝርዝሮችና
- ያገኙዋቸውን ሽልማቶችና የማዕረግ ዕድገት በበቂ ሁኔታ የቀረበበት ታሪክ ስለሆነ ነው፡፡

ትክክለኛነት (እውነተኛነትን) በሚመለከት በጥናቴ በገጽ 23 እንዳመለከትኩት የምክንያትና የውጤት ጣጣን ያካተተ፣ መቼቱንም ያገናዘበ መረጃ በበቂ ሁኔታ የያዘ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ምክንያቱም ታሪኩ ኢ-ልቦለዳዊ የጽሑፍ ዘርፍ ነው፡፡

ከላይ በተገለጹት ጉዳዮች ተመርኩዤ የሚከተሉትን አሉታዊና አዎንታዊ ጐኖች ፈትሼ አግኝቻለሁ፡፡

**በአሉታዊ (በድክመት) ጐን፤**

- ✓ ባለታሪኩ ከግለ-ታሪኩ ጋር ተያያዥነት የሌለው ሰፊ ሐተታ ገጽ (168 — 171) ማቅረባቸው የምክንያትና የውጤት መድበስበስ አስከትሏል፡፡ ለምሳሌ የጦሩ በቡድን

መወያየት በየምሽጉ ስለሚደረገው ፕሮፓጋንዳ ጸረ-ፕሮፓጋንዳ ያነሱት ሐተታ የግለ-ታሪኩን ትክክለኛነት አጎድሏል፡፡

**በተጨማሪም፤**

- ስለትምህርት ቤት ሕይወታቸው /ገጽ 1 – 2/ ያቀረቡት ሐሳብ ከቄስ ትምህርት ቤት እስከ መንግሥት ትምህርት ቤት የነበረውን ሁኔታ ያካተቱበት መንገድ በዚያን ጊዜ ትምህርት ቤቶች ካለመስፋፋታቸው ጋር ተያይዞ ሲታይ የምክንያትና ውጤት ሁኔታ የተከተለ አዎንታዊ የሆነ አቀራረብ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡

ተአማኒነት ሲባል ደግሞ የቀረበው ታሪክ ያለው ተቀባይነት ደረጃ፣ በነባራዊ መረጃ ተደግፎ መቅረቡ በምዕራፍ ሶስት ተጠቅሷል፡፡ ከዚህም በመነሳት

- ❖ በፎቶግራፍ ተደግፈው የቀረቡት ሃሳቦች አንዳንዶቹ ጥራት እንደሚጎድላቸውና
- ❖ በገጽ 267 'የመከላከያ ሚኒስትሩ' ጉብኝት የሚለው ጊዜው (ዓመተምህረት) ስላልተመለከተላቸው ተአማኒነት ይጐላቸዋል፡፡

በአንጻሩ ጄኔራሉ ስለደረሳቸው የምስጋና ደብዳቤ በገጽ 62 ላይ የቀረበውና ከገጽ 312 – 314 በሶስት ዘመቻዎች ስላደረጉት አስተዋጽኦ የተጻፈላቸው የምስጋና ደብዳቤ በፎቶኮፒ የተደገፈ ግልጽ መረጃ ስላላቸው ተአማኒ ናቸው፡፡

### 4.2 ጥቆማ

በማጠቃለያው ላይ በተነሱ ሃሳቦችና በመጸሐፉ ውስጥ ባሉ ድክመቶችና ጠንካራ ጐኖች ላይ በመመርኰዝ የሚከተለውን አቅርቤያለሁ፡፡

- ጸሐፊው ታሪካቸውን ሲያቀርቡ ዝርዝር ጥቃቅን ነገሮችን በብዛት ከማቅረብ ይልቅ ተፈላጊዎቹን ነገሮች መርጠውና መጥነው ቢያቀርቡ፡፡
- ባለታሪኩ ያቀረቧቸው መረጃዎችና ጊዜ ያልተጠቀሰላቸው መረጃዎች ከተሰሩበት የጊዜ ክልል ጋር ተጣጥመው በተሻለ መንገድ ቢቀርቡ፡፡
- ማንኛውም ግለ-ታሪኩን ለመጻፍ የሚነሳ ሰው ታሪኩን በትክክለኛ መረጃ ላይ ተመርኩዞ፣ ስለዘርፉ አውቆና የመስኩን ምሁራን ሃሳበ አግኝቶ ቢጽፍ ሥራው የተሻለ እንደሚሆን ባይዘነጋ፡፡

- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለግለ-ታሪክ አጻጻፍና አዘገጃጀት ትኩረት ቢሰጡና በሀገራችን ግለ-ታሪክን ጽፎ ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ ቢለመድ፡፡
- ግለ-ታሪክ በተዋቂ ሰዎችና በነገሥታት ታሪክ ላይ ብቻ አተኩሮ ባይጻፍ፣ የተለያዩ ለወገኖቻቸውና ለሀገራቸው መልካም ተግባር የሰሩ ሰዎችን ታሪክ እንድናውቅ ጥረት ቢደረግ፡፡

# ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

1. A biography of one self written by that person only is called auto biography
2. An auto biography is when a person writes about him self or her self as oppose to another person writing about them. Then it's considered a biography
3. A biography is an account of the life of a person written produced or composed by another. It is a piece of non-fictional literature. It is reported that the first instants of biographical writing were inscriptions and funeral speeches.
4. An autobiography is information about one's own life written by that one person in it, it tells what that person's life is all about when writing your own auto biography, use interesting facts to explain as much about your self as you can
5. When writing an auto biography you focus on three major things: Who you are in life, what life means to you and what your out look on the future is.

# ዋቢ መጻሕፍት


- ሳህለስላሴ ብርሃነማርያም፣ ሹክታ፣ አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ቤት፣ 1992

- ብ/ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተማርያም፣ የጦርሜዳ ውሎ፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ 1997

- አማኑኤል አብርሃም፣ የሕይወቴ ትዝታ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣ 1992

- አጼ ኃይለስላሴ፣ ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1929

- ደረጄ ገብሬ፣ ተግባራዊ የጽሕፈት መማሪያ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1996

- http: //en. wikipedia. org/wiki/ Biography

- http: //WWW. Writers services.com/mag/05/ writing Bio-auto-bio./htm

- Mac Henry, Robert the New Encyclopedia Britannica Vol.2 Chicago Encyclopedia

- Literate, Ure, the Cambridge Encyclopedia New York, Com

- የትናየት አንዳርጌ፣ "የቀደምት ሴት ጋዜጠኞችን የሕይወት ታሪክና ሥራዎቻቸው" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ዲማጽ)፣1989

- ብርሃን ክብረት፣ "የአርቲስት አለባቸው ተካ የሕይወት ታሪክና ሥራዎቹ፣" በአ.አ.ዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ክፍል፣ 1998 ዓ.ም

- ጥላሁን በሻህ፣ "ከ1967 — 1983 በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የሕይወት ታሪካቸው የተጻፈላቸው ኢትዮጵያውያን/ት መዘርዝር፣" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ዲማጽ) ፣1989

- ፀጋዬ ገ/ማርያም፣ "የአለልኝ መካንንት የሕይወት ታሪክ እና ሥራዎች፣" በአ.አ.ዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ክፍል (ድማጽ፣ 1992